## የመጀመሪያዪቱ ፡ የዮሐንስ ፡ መልእክት ።

፪ኛ ፡ የሚጽፍ ፡ ነውና ፡ ቀዳማዊ ፡ አለ ። ዮሐንስ ፡ መሢሕ ፡ እያለ ፤ ሲያስተምር ፡ ስምቶ ፡ ድምጥያኖስ ፡ አሥሮ፡ አግዞታል፤ ዛሬስ ፡ በላዬ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ያነግሥብ ኛል ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ነው ፡ ኋላ ፡ እሱ ፡ ሞተ ፡ ወነግሠ፡ ወልዱ ፡ ጠራ ብያኖስ ፡ ይላል ፡ ልጁ ፡ ጠራብያኖስ ፡ ነገሠ ፡ (አራጥያኖስም ፡ ይላል) ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ የኛማ፡ መምህር፡ የሚያስተ ምርለት ፡ ምድራዊ፡ እንጅ፡ ያይደለ፡ ሰማ ያዊ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ሲያስተምሩ ፡ ሰም ቶ ፡ ምድራዊ ፡ ካልሆነ ፡ ሰማያዊ ፡ ከሆነ ፡ ምን ፡ ዕዳዬ ፡ ብሎ ፡ በሰባት ፡ ዓመቱ ፡ ፈቶታል ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ግን ፡ ያላ ፈሉት ፡ ክህደት ፡ የለም ፡ ደቀ ፡ መዝሙ ር ፡ ከመምህሩ ፡ ከተለየ ፡ ክህደት ፡ ማግ ኃት ፡ ልማዱ ፡ ነውና ፡ ሙቶ ፡ አልተነ ሣም ፡ ሙቶ ፡ የተነሣው ፡ ቀዳማዊ ፡ አይ ደለም ፡ በብርሃን ፡ የሚሠራውን ፡ እንጅ ፡ በጨለማ ፡ በነቢብ ፡ በገቢር ፡ የሚሠራ ውን ፡ እንጅ ፡ በሐልዮ ፡ የሚሠራውን ፡ አያውቅም ፡ ብለውታል ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ካመኑ፡ ከተጠመቁ ፡ ሌላ፡ ምን ፡ ምግባር፡ ያሻል ፡ ብለዋል ፡ ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ይጽፋል፤ (ምክንያት) ፡ ንዜንወክሙ። በእንተ ፡ ው እቱ ፡ ዘሀሎ ፡ እምቅድም ፡ ውእቱ ፡ ዘሰ ማዕናሁ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፩ ፡ (በል) ። ወንዜንወ ክሙ ፡ ንሕነ ፡ ሕይወተ ፡ እንተ ፡ ለዓለም ፡ በል ፡ ቍ ፡ ፪ ። ወንዜንወክሙ ፡ ለክሙኒ ፡ ከመ ፡ አንትሙኒ፡ በል፡ ቍ፡ ፫። ወንዜንወ ክሙ፡ከመ፡እግዚአብሔር፡ብርሃን፡ውእቱ፡ በል ፡ ፭ ። ወደሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያነጽሐነ ፡ በል ፡ ፯ ። ወእመሰ ፡ ንብል ፡ አልብነ ፡ ኃጢአት ፡ በል ፡ ፰ ። ደቂቅየ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዛቲ ፡ ሰዓት ፡ ደኅሪት ፡ ይእቲ ፡ በል ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፲፰ ። አኃዊነ ፡ ለኵላ ፡ መንፈስ ፡ ኢት እመንዋ ፡ በል ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፩ ። ወአልቦ ፡ ፍርሀት ፡ ውስተ ፡ ተፋቅሮትነ ፡ በል ፡ ፲፰ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በውኃ ፡ እያጠበ ፡ በደሙ ፡ እያነጻ ፡ በልጅነት ፡ እያከበረ ፡ እንዲሄድ ፡ ያመጣል ፡ ወመኑ ፡ ውእቱ ፡ ዘይመውእ ፡ ለዓለም፡ በል፡ ም ፡ ፭ ፡ ፫ ። ወእመሰ፡ ቦ ፡ ዘርእዮ ፡ ለካልኡ ፡ በል ፡ ፲፯ ። የጻፈበት ፡ ሀገር፡ በመካከል፡ ክታብ፡ ወሳጅ፡ የለም ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፤ ንዜንወክሙ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘሀሎ ፡ እም ቅድም ፡

በቅድምና ፡ የነበረ ፡ የሱን ፡ የቅድምናው ን ፡ ነገር ፡ እንነግራችኋለን ፡

ውእቱ ፡ ዘሰማዕናሁ ፡ በእዘኒነ ፡

የቅድምናውን ፡ ነገር ፡ ሲናገር ፡ የሰማ ነው ፡ እሱ ፡ ነው ፤ እምቅድመ ፡ ይትወ ለድ፡ አብርሃም፡ ሀሎኩ ፡ አነ ፡ ብሎ፡ እም ቅድመ ፡ ይትወለድ ፡ አብርሃም ፡ ሀሎኩ ፡ አነ ፡ ያለውን ፡ የቅድምናውን ፡ ነገር ፡ በ ሥራው ፡ ለማስረዳት ፡

ወዘርኢናሁ ፡ በአዕይንቲነ ፡

በደረቅ ፡ ግምባር ፡ ዐይን ፡ ሲፈጥር ፡ ያየ ነው ፡ እሱ ፡ ነው ፡

ወዘጠየቅናሁ ፡ ወዘገሠሠሣሁ ፡ እደዊነ ፡ በእንተ ፡ ነገረ፡ ሕይወት ።

ቅድምናውን ፡ ስለማወቅ ፡ በጃችን ፡ ዳሰ ን ፡ የተረዳነው ፡ እሱ ፡ ነው ። ሐተታ ፡ ቶማስ ፡ ጐኑን፡ በዳሰሰው ፡ ጊዜ ፡ እጁን ፡ ከእሳት ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ጅማት ፡ አድርጎ ታል ፡ እሱም ፡ እግዚእየ ፡ ወአምላኪየ ፡ ብሏል ፤ መዳሰሱን ፡ ሲያይ ፡ እግዚእየ ፡ ማቃጠሉን ፡ ሲያይ ፡ አምላኪየ ፡ ብሏል ፤ ይህንም ፡ ሊቁ ፡ አንተ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ወአ ንተ ፡ ዘይእዜ ፡ ብሎ ፡ ወስዶታል ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ። ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፴፱ ።

፪ ፤ እስመ ፡ ሕይወት፡ ተዐውቀት፡ ለነ ፡ ወርኢናሃ፡

ቅድምና፡ ታውቃለችና፡ ተረድታናለችና፡

ወስምዐ ፡ ኮነ ፡

መሰክርናት ፡ ቀዳሚሁ ፡ ቃል ፡ ውእቱ ፡ ብለን ።

ወንዜንወክሙ ፡ ለክሙኒ ፡ ንሕነ ፡ ሕይወተ ፡ እንተ ፡ ለዓለም ፡ እንተ ፡ ሀለወት ፡ ኀበ ፡ አብ ።

(ጥቅ) ፡ አሐቲ ፡ ቅድምናሆሙ ፡ ለሥላሴ ፡ ወዕሩያን ፡እሙንቱ ፡ በቅድምና፡ እንዲል ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፡ የምትሆን ፡ ቅድምና ፡ የዘለ ዓለም፡ ድኅነት፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ እንነግራ ችኋለን ፡ ወዘሂ ፡ ኮነ ፡ በእንቲኣሁ ፡ ቦቱ ፡ ሕይወት ፡ ውእቱ ፡ ብለን ፡

ወተዐውቀት ፡ ለነ ።

ቅድምና ፡ ታውቃልናለች ፡ ተረድታልና ለችና ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፬ ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፩ ።

፫ ፤ ወርኢናሃ ፡ ወሰማዕናሃ ፡

አነ ፡ ውእቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወደኃራዊ ፡ ዘሕ ያው ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ሲል ፡ ከቃሉ ፡ ሰምተናታልና። አንድም ፡ (ንዜንወክሙ)፡ በቅድምና፡ የነበረ፡ የእሱ፡ የህልውናውን ፡ ነገር ፡ እንነግራችኋለን ፡ (ውእቱ ፡ ዘሰማ ዕናሁ ፡ በእዘኒነ) ፡ አነ ፡ በአብ ፡ ወአብ ፡ ብየ ፡ አነ ፡ ወአብ ፡ አሐዱ ፡ ንሕነ ፡ ብሎ ፡ ሲያስተምር ፡ የሰማነው ፡ እሱ ፡ ነው ፤ ወዘርኢናሁ ፡ በአዕይንቲነ ፡ እስመ ፡ ስም ዐ ፡ ቃላቲሁ ፡ ምግባሩ ፡ ውእቱ ፡ እንዲል፡ አነ ፡ በአብ ፡ ወአብ ፡ ብየ ፡ አነ ፡ ወአብ ፡ አሐዱ ፡ ንሕነ ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ የህ

www.ethiopianorthodox.org



ልውናውን ፡ ነገር ፡ በሥራው ፡ ለማስረ ዳት ፡ የአራት ፡ ቀን ፡ ሬሳ ፡ አላዛርን ፡ የዕ ለት ፡ ሬሳ ፡ ወለተ ፡ ኢያኢሮስን ፡ ወልደ ፡ መበለትን ፡ ሲያስነሣ ፡ ያየነው ፡ እሱ ፡ ነው ። ወዘጠየቅናሁ ፡ ወዘገሠሣሁ ፡ እደ ዊነ ፡ በእንተ ፡ ነገረ ፡ ሕይወት ። ህልውና ውን፡ስለማወቅ፡ በቃላችን፡ ጠይቀን፡የተረ ዳነው ፡ እሱ ፡ ነው፡(ጥቅ)፡ሀሎኑ ፡ እዴሁ ፡ ለኢዮአብ ፡ በዝ ፡ ነገርኪ ፡ በእደ ፡ ሙሴ ፡ በእደ ፡ ካህናት ፡ እንዲል ። ሐተታ ፡ ፊል ጶስ፡ አርእየነሁ ፡ ለአብ ፡ ወየአክለነ ፡ ቢ ለው ፡ ዘመጠነ፡ ዝ ፡ መዋዕል፡ ሀሎኩ፡ ም ስሌክሙ ፡ ኢያእመርከኒኑ ፡ ፊልጶስ ፡ ዘር እየ ፡ ኪያየ ፡ ርእዮ ፡ ለአቡየ ፡ ብሎታል ፡ (እስመ ፡ ሕይወት ፡ ተዐውቀት ፡ ለነ) ፡ ህልውና ፡ ታውቃልናለችና ፡ ተረድታ ናለችና ። (ወስምዐ ፡ ኮነ) ፡ መሰክርናት ፤ ወውእቱ ፡ ቃል ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ብለን ። ወንዜንወክሙ ፡ ንሕነ ፡ ሕይወተ። ነአምን ፡ ከመ ፡ አብ ፡ ህልው ፡ በወልድ ፡ ወበመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወነአም ን ፡ ከመ ፡ ወልድ ፡ ህልው ፡ በአብ ፡ ወበ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወነአምን ፡ ከመ ፡ መን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ህልው ፡ በአብ ፡ ወበወል ድ ፡ ህልዋን ፡ እሙንቱ ፡ በአብ ፡ እንዘ ፡ ይሄልው ፡ በበአካላቲሆሙ ፡ እንዲል ፡ ከአብ ፡ ዘንድ ፡ የምትሆን ፡ ህልውና ፡ የዘለዓለም፡ ድኅነት፡ እንደ፡ ሆነች ፡ እንነግ ራችኋለን ፤ ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ሕይወት ፡ ዘ ለዓለም ፡ ከመ ፡ ያእምሩከ ፡ ለከ ፡ ለ፩ ፡ አ ምላክ ፡ ጽድቅ ፡ ብሏል ፤ ብለን ። (ወተዐ ውቀት ፡ ለነ ፡ ወርኢናሃ) ፡ ህልውና ፡ ታ ውቃልናለች ፡ ተረድታናለችና ፤ (ወሰማ ዕናሃ) ፡ ወበከመ ፡ ዘፈነወኒ ፡ አብ ፡ ሕያ ው ፡ አነኒ ፡ ሕያው ፡ በእንተ፡ አብ ፡ ብሎ፡ ሲያስተምር ፡ ከቃሉ ፡ ሰምተናታልና።አን ድም ፡ ንዜንወክሙ ፡ በቅድምና ፡ የነበረ ፡ የእሱን ፡ የሥጋዌውን፡ ነገር፡ እንነግራችኋ ለን ፤ (ውእቱ ፡ ዘሰማዕናሁ) ፡ ወፃእኩ ፡ እምአብ ፡ ወመጻእኩ ፡ አቡየ ፡ ፈነወኒ ፡ ወአነ ፡ ተፈኖኩ ፡ ብሎ ፡ ሲናገር ፡ የሰማ ነው ፡ እሱ ፡ ነው ። (ወዘርኢናሁ) ፡ ባጭ ር ፡ ቁመት ፡ በጠባብ ፡ ደረት ፡ ተወስኖ ፡ ሲያስተምር ፡ ያየነው ፡ እሱ ፡ ነው ። (ወ ዘገሠሣሁ) ፡ በጃችን ፡ ዳሰን ፡ የተረዳነው ፡ እሱ ፡ ነው ። ሐተታ፡ ሦስት፡ ዓመት ፡ ከሦ ስት ፡ ወር ፡ አብሯቸው ፡ ሲኖር ፡ በማና ቸው ፡ ምክንያት ፡ ይዳስሱት፡ ነበረና ፡ (እ ስመ፡ ሕይወት)፡ሥጋዌ፡ታውቃልናለችና፡ (ወስምዐ፡ ኮነ)፡መሰክርናት፡ውእቱ፡ ቃል፡ ሥጋ ፡ኮነ፡ ብለን፡ እስመ፡በፈቃዱ፡ ወበሥ ምረተ፡አቡሁ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡መጽአ፡እ ንዲል።(ወንዜንወክሙ)፡ በአብ ፡ ፈቃድ፡ የምትሆን ፡ ሥጋዌ፡ የዘለዓለም ፡ ድኅነት፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ እንነግራችኋለን ፡ እስመ ፡ ኢፈነዎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለወልዱ ፡ ውስ ተ ፡ ዓለም ፡ ከመ ፡ ይኰንኖ ፡ ዘእንበለ ፡ ከመ ፡ ይሕየው ፡ ዓለም ፡ በእንቲአሁ ፡ ብ ሏል ፡ ብለን ። ወተዐውቀት ፡ ሥጋዌ ፡ ታውቃልናለች ፡ ተረድታናለችና ፡ (ወር ኢናሃ ፡ ወሰማዕናሃ)፡ አንሰኬ ፡ መጻእኩ ፡ ከመ ፡ ይርከቡ ፡ ሕይወተ ፡ ዘለዓለም ፡ ወ ፈድፋደ ፡ ይርከቡ ፡ ሲል ፡ ከቃሉ ፡ ሰምተ ናታልና ። አንድም ፡ ንዜንወክሙ ። በቅ ድምና ፡ የነበረ ፡ የእሱን ፡ የትንሣኤውን ፡ ነገር ፡ እንነግራችኋለን ፡ (ውእቱ ፡ ዘሰማ ዕናሁ) ፡ ናሁ ፡ ነዐርግ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሲል የሰማነው ፡ እሱ ፡ ነው ። (ወዘርኢናሁ) ፡ በዝግ ፡ ደጅ ፡ ገብቶ ፡ ሰላም ፡ ለክሙ ፡ ሲል ፡ ያየነው ፡ እሱ ፡ ነው ። (ወዘጠየቅ ናሁ ፡ ወዘገሠሣሁ) ፡ ትንሣኤውን ፡ ስለ ማወቅ ፡ በጃችን ፡ ዳሰን ፡ የተረዳነው ፡

እሱ ፡ ነው ። ሐተታ ፡ በዝግ ፡ ደጅ ፡
ገብቶ ፡ ሰላም ፡ ለክሙ ፡ ብሏቸዋል ፤ ወመ
ስሎሙ ፡ ከመ ፡ ዘመንፈስ ፡ ይሬእዩ ፡ ይ
ላል ፡ ምትሐት ፡ መስሏቸው ፡ ደንግጠ
ዋል ፤ ምንትኑ ፡ ያፈርሃክሙ ፡ አነ ፡ ውእ
ቱ ፡ ርእዩ ፡ እደውየ ፡ ወእገርየ ፡ ወግሥሡ
ኒ ፡ ወአእምሩ ፡ ከመ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ እስ
መ ፡ ለመንፈስሰ ፡ አልቦቱ ፡ ሥጋ ፡ ወአ
ፅም ፡ በከመ ፡ ትሬእዩኒ ፡ ብሏቸዋል ፤
(እስመ ፡ ሕይወት) ፡ ትንሣኤ ፡ ታውቃ
ልናለችና ፡ (ወርኢናሃ) ፡ አውቀናታል ፡
ተረድተናታልና ፡ (ወስምዐ፡ኮነ) ፡ መስከር
ናት፡ ንሥትም፡ ለዝንቱ፡ቤተ፡ መቅደስ፡ ያለ
ውን፡ ውእቱስ ፡ ይቤሎሙ፡ በእንተ፡ ቤተ ፡
ሥጋሁ፡ብለን። (ወንዜንወክሙ) ፡ ወነበረ፡
በየማነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡሁ፡ እንዲል፡
በአብ ፡ ዘንድ ፡ ታውቃ ፡ ያለች ፡ ትንሣኤ፡
ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ሕይወት ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡
እንነግራችኋለን ፤ ለእመ ፡ ኢወድቀት ፡
ኅጠተ ፡ ሥርናይ ፡ ወኢሞተት ፡ ባሕቲታ፡
ትነብር ፡ ወእመሰ ፡ ሞተት ፡ ብዙኀ ፡ ፍሬ፡
ትፈሪ ፡ ብሏል ፡ ብለን ፡ (ወተዐውቀት) ፡
ትንሣኤ ፡ ታውቃልናለችና ፡ (ወርኢናሃ) ፡
አውቀናታል ፡ ተረድተናታልና ፡ (ወሰማ
ዕናሃ) ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ትንሣኤ ፡ ወሕይ
ወት ፡ ሲል ፡ ከቃሉ ፡ ሰምተናታልና ፡

ወንዜንወክሙ ፡ ለክሙኒ ፡ ከመ ፡ አንትሙኒ ፡ ትኩኑ ፡
ሱታፌ ፡ ምስሌነ ።

እናንተም ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ትሆኑ ፡
ዘንድ ፡ አንድ ፡ ሁኑ ፡ ብለን ፡ እንነግራች
ኋለን ፡

ወሱታፌነሰ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ወምስለ ፡ ወልዱ ፡ ኢየ
ሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ከናንተ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ መሆን ፡ እንደ ፡
ምን ፡ ነው ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከኛስ ፡
ጋራ ፡ በሃይማኖት ፡ አንድ ፡ መሆን ፡ ከእግ
ዚአብሔር ፡ አብ ፡ ከባሕርይ ፡ ልጁ ፡ ከኢ
የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ መሆን ፡
ነው። አንድም ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ በሃይማኖት ፡
በልጅነት ፡ አንድ ፡ ትሆኑ ፡ ዘንድ፡ አንድ፡
ሁኑ ፡ ብለን ፡ እንነግራችኋለን ፡ ከናንተ ፡
ጋራ ፡ በሃይማኖት ፡ በልጅነት ፡ አንድ ፡
መሆን፡ ምን ፡ ይረባል፡ ምን ፡ ይጠቅማል ፡
ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከኛ ፡ ጋራስ ፡ በሃይ
ማኖት ፡ በልጅነት ፡ አንድ ፡ መሆን ፡ የሚ
ናቅ ፡ አይደለም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡
ከባሕርይ ፡ ልጁ ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ጋራ ፡ አንድ ፡ መሆን ፡ ነው ።

፬ ፤ ወዘንተ ፡ ንጽሕፍ ፡ ለክሙ፡ ከመ ፡ ትፍሥሕት
ክሙ ፡ ፍጽምተ ፡ ትኩን ።

ይህንንም ፡ እንጽፍላችኋለን ። (ትፍሥሕ
ትክሙ፡ ፍጽምተ ፡ ትኩን ፡ ብነ) ፡ ተድላ ፡
ደስታችሁ ፡ በኛ ፡ ፍጹም ፡ ትሆን ፡ ዘን
ድ ። ሐተታ ፡ ቀድሞ ፡ ሲያስተምሯቸው ፡
መከራ ፡ እየተቀበሉ ፡ ነው ፡ ኋላም ፡ ክታ
ብ ፡ ጽፈው ፡ ሲሰዱላቸው ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡
እንጅ ፡ ለኛ ፡ ብለው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ደስ፡
ይላቸዋልና ። አንድም ፡ ትፍሥሕትነ ፡
ፍጽምተ ፡ ትኩን ፡ ብክሙ ፡ ተድላ ፡ ደስ
ታችን ፡ በናንተ ፡ ፍጹም ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡
ቀድሞ ፡ ሲማሩላቸው ፡ ሲያምኑላቸው ፡
ሲጠመቁላቸው ፡ ኋላም ፡ ክታብ ፡ ጽፈ
ው ፡ ሰደውላቸው ፡ ሲቀበሏቸው ፡ ደስ ፡
ይላቸዋልና ፡ ትኩኑ ፡ ሱታፌ ፡ ምስሌነ ፡
ወሱታፌነሰ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ላለው ፡ አመ
ጣ ፡ ዮሐ ፡ ፲፰ ፡ ፲፩ና ፡ ፲፯ ፡ ፳፬ ።

፭ ፤ ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ዜና ፡ እንተ ፡ ሰማዕናሃ ፡ ትካት፡
እምኔሁ ፡

ይህችም፡ በጥንት፡ ስብከት ፡ ከእሱ ፡ የሰ
ማናት ፡ ትምህርት ፡ ናት ፤ (ትኩኑ ፡ ሱታ
ፌ ፡ ምስሌነ ፡ ብሎ ፡ ነበረና ፡ ከመ ፡ ይኩ



ኑ፡ አሐደ ፡ ብነ ፡ ከማነ፡ዘኪያክሙ ፡ ተወ
ከፈ ፡ ኪያየ ፡ ተወክፈ ፡ ሲል ። አንድም ፡
ከመ ፡ ትፍሥሕትክሙ ፡ ፍጽምተ ፡ ትኩ
ን ፡ ላለው ፡ ወዘንተ ፡ እነግር ፡ ለዓለም ፡
ከመ ፡ ፍሥሓየ ፡ ይኩን ፡ ፍጹመ ፡ በላዕ
ሌሆሙ ፡ ሲል ፡ የሰማናት ፡ ትምህርት ፡
ይህች ፡ ናት ፡

ወንዜንወክሙ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብርሃን ፡
ውእቱ ።

(በብርሃን ፡ እንጅ ፡ በጨለማ ፡ የሚሠራ
ውን ፡ አያውቅም ፡ ላሉት) ፡ ጻድቅ ፡ ምእ
መን ፡ ዕውቀት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡

ወጽልመትሰ ፡ አልቦ ፡ ኀቤሁ ፡ ወኢአሐቲኒ ፡

ኃጢአት ፡ ድንቁርና ፡ ግን ፡ በሱ ፡ ዘንድ ፡
ጥቂትስ ፡ እንኳ ፡ (አሐተኒ) ፡ አንድ ፡ ወገ
ንስ ፡ እንኳ ፡ እንደሌለበት ፡ እንነግራች
ኋለን ፡ መዝ ፡ ፺፩ ፡ ፱ ። ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፲፱ ።

፮ ፤ ወእመሰ ፡ ብነ ፡ ሱታፌ ፡ ምስሌሁ ፡ ንቤለክሙ፤

ከእሱ፡ ጋራ፡ አንድነት፡ አለን፡ ብንላችሁ ፡

ወውስተ ፡ ጽልመት ፡ ነሐውር ፡

እኛ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ኃጢአት ፡ ወደ ፡ ክህ
ደት ፡ ብንሄድ ፡

ንሔሱ ፡

ሐሰት ፡ እንናገራለን ፡

ወኢንገብራ ፡ ለጽድቅ ፡ ወለርትዕ ።

ጽድቅ ፡ ርትዕንም ፡ አንሠራትም ፡ ም ፡
፪ ፡ ፬ ።

፯ ፤ ወእመሰ ፡ ውስተ ፡ ብርሃን ፡ ነሐውር ፡ በከመ ፡
ውእቱ ፡ ብርሃን ።

እሱ ፡ ጻድቅ ፡ ምእመን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሃ
ይማኖት ፡ በጽድቅ ፡ ብንኖር ፡ ግን ፡

ሱታፌን ፡ ንሕነ ፡ በበይናቲነ ፡

ሁላችን ፡ ከእሱ ፡ ጋራ ፡ አንድ፡ ነን፡ ወደ
ሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ማንሻ ፡ አን
ድም ፡ (ወንዜንወክሙ ፡ ብለሀ ፡ መልስ) ፡
(እመሰ ፡ ንቤለክሙ)፡ ከእሱ፡ ጋራ፡ አንድ፡
ነን ፡ ብንላችሁ ፡ (ወውስተ ፡ ጽልመት) ፡
እሱን፡አላዋቂ፡ ብንለው፡ ሐሰት፡ እንናገራ
ለን ፡ ጽድቅ ፡ ርትዕንም ፡ አንሠራትም ፡
እሱ ፡ ዐዋቂ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ እንደ፡ መሆኑ ፡
ዐዋቂ ፡ ብንለው ፡ ግን ፡ እርስ ፡ በርሳ
ችን ፡ አንድ ፡ ሁነን ፡

ወደሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያነጽሐነ ፡ እምኵሉ ፡
ኃጣውኢነ ።

የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥጋው ፡ ደሙ ፡
ከኃጢአታችን ፡ ያነጻናል ። ሐተታ ፡ ም
ነው ፡ የምንነጻ ፡ በጥምቀት ፡ አይደለም ፡
ቢሉ ፡ ከላይ ፡ ነቁ ፡ አንድ ፡ ነውና ፡ ያን ፡
ሲያይ ። አንድም ፡ ከጥምቀት ፡ በፊት ፡
የሚሠራ ፡ ኃጢአት ፡ በጥምቀት ፡ ይሠረ
ያል ፡ ከጥምቀት ፡ በኋላ ፡ የሚሠራ ፡ ኃጢ
አት፡ግን፡ በሥጋው፡ በደሙ፡ ይሠረያልና፤
(ጥቅ) ፡ ኃጢአት ፡ ዘእምቅድመ ፡ ጥምቀ
ት ፡ ይሠረይ ፡ በጥምቀት ፡ ወኃጢአት ፡
ዘእምድኅረ ፡ ጥምቀት ፡ ይሠረይ ፡ በሥጋ
ሁ ፡ ወደሙ ፡ እንዲል ። አንድም ፡ ካልታ
ወቀው ፡ ከደጋጉ ፡ ከጥቃቅኑ ፡ ኃጢአት።

፰ ፤ ወእመሰ ፡ ንብል ፡ አልብነ ፡ ኃጢአት ፡ ንጌጊ ።
ለርእስነ ።

በድለን ፡ አልበደልንም ፡ ብንል ፡ ራሳች
ነን ፡ ለመጉዳት ፡ እንስታለን ።

ወአልቦ ፡ ርትዕ ፡ ኀቤነ ።

በኛ ፡ ዘንድ ፡ ዕውነት ፡ የለም ።

፱ ፤ ወእመሰ ፡ ነገርነ ፡ ወአመነ ፡ ኃጢአትነ ፡

በድለን ፡ በድለናል ፡ ብንል ፡ ግን ፡

ምእመን ፡ ውእቱ ፡ ወጻድቅ ፡ ከመ ፡ ይኅድግ ፡ ለነ ።
ኃጣውኢነ ፡

ኃጢአታችንን ፡ ይቅር ፡ ይለን ፡ ዘንድ ፡
የታመነ ፡ ቸር ፡ የባሕርይ፡ አምላክ፡ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ወያነጽሐነ ፡ እምኵሉ ፡ ጌጋይነ ።

ከኃጢአታችን ፡ ሁሉ ፡ ያነጻናል ፡ ም፡፳፰፡ ፲፫ ። ፩ ፡ ተሰ ፡ ፭ ፡ ፳፱ ።

፲ ፤ ወእመሰ ፡ ንቤ ፡ ኢአበስነ ፡ ሐሳዌ ፡ ንሬስዮ ፡ ለቶቱ ፡

በድለን ፡ አልበደልንም ፡ ብንል ፡ ግን ፡ ቦሁ ፡ ዘይሜወር ፡ እምኔየ ፡ እምኔየሁ ፡ ይሜወር ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ዘእፈትን ፡ ልበ ፡ ወኵልያተ፡ አነ፡ ውእቱ፡ ብርሃኑ፡ ለዓለም፡ ያለ ፡ እሱን ፡ ሐሰተኛ ፡ እናደርገዋለን ፡

ወቃሉኒ ፡ ኢሀሎ ፡ ኀቤነ ።

ቦሁ ፡ ዘይሜወር ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ዘእፈትን፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ብርሃኑ ፡ ለዓለም ፡ ያለው ፡ ቃሉ ፡ በኛ ፡ ጸንቶ ፡ አይኖርም። አንድም ፡ (ወእመሰ ፡ ንብል) ፡ ጥንቱን ፡ ኃጢአት ፡ አልሠራንም ፡ ብንል ፡ ራሳችንን ፡ ለመጉዳት ፡ እንስታለን ። (ወአልቦ ፡ ርትዕ) ፡ ዕውነት ፡ ነገርም ፡ ከኛ ፡ ዘንድ ፡ የለም ፡ (ወእመሰ ፡ ነገርነ ፡ ኃጢአተነ) ፡ በድለናል ፡ ብንል ፡ ግን ፡ ኃጢአታችንን ፡ ያስተሠርይልን ፡ ዘንድ ፡ የታመነ ፡ ቸር ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ከኃጢአታችንም ፡ ያነጻናል ። (ወእመሰ ፡ ንቤ ፡ ኢአበስነ) ፡ ጥንቱን፡አልበደልንም፡ብንል፡ግን፡(ሐሳዌ፡ ንሬስዮ) ፡ ኵሉ ፡ አበሰ ፡ መኑ ፡ ዘይነጽሕ ፡ እምኃጢአት ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ብርሃኑ ፡ ለዓለም ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ዘእፈትን ፡ ልበ ፡ ወኵልያተ ፡ ቦሁ ፡ ዘይሜወር ፡ እምኔየ ፡ እምኔየሁ ፡ ይሜወር ፡ ያለ ፡ እሱን ፡ ሐሰተኛ ፡ እናደርገዋለን ። (ወቃሉኒ) ፡ ኵሉ ፡ አበሰ፡ መኑ ፡ ዘይነጽሕ ፡ እምኃጢአት ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ብርሃኑ ፡ ለዓለም ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ዘእፈትን ፡ ልበ ፡ ወኵልያተ ፡ ቦሁ ፡ ዘይሜወር ፡ እምኔየ ፡ እምኔየሁ ፡ ይሜወር ፡ ያለው ፡ ቃሉም ፡ በኛ ፡ ጸንቶ ፡ አይኖርም።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ ፤ ደቂቅየ ፡ ዘንተ ፡ እጽሕፍ ፡ ለክሙ ፡ ከመ ፡ ኢተአብሱ ፡

ጸሐፍኩ ፡ ለክሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ሙቶ ፡ አልተነሣም ፡ ሙቶ፡ የተነሣው፡ ቀዳማዊ ፡ አይደለም ፡ እንዳትሉ ፡ ንዜንወክሙ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘሀሎ ፡ እምቅድም ፡ ላለው፡ በብርሃን፡ የተሠራውን ፡ እንጅ ፡ በጨለማ ፡ የተሠራውን ፡ አያውቅም ፡ እንዳትሉ ፡ ንዜንወክሙ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብርሃን ፡ ውእቱ ፡ ላለው ፡ በድላችሁ ፡ አልበደልንም ፡ እንዳትሉ ፡ ወእመሰ ፡ ንብል ፡ አልብነ ፡ ኃጢአት ፡ ንጌጊ፡ ለርእስነ ፡ ብዬ ፡ ጻፍሁላችሁ ። አንድም ፡ ለሚመጣው ፡ ብንመለስስ ፡ ኃጢአታችንን ፡ ማን ፡ ያስተሠርይልናል ፡ እንዳትሉ ፡ (እጽሕፍ ፡ ለክሙ) ፡ እጽፍላችኋለሁ ።

ወእመኒ፡ ቦ ፡ ዘአበሰ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ ብነ፡ ኀበ ፡ አብ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

በድሎ ፡ ንስሓ ፡ የገባ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ኃጢአታችንን ፡ የሚያስተሠርይልን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከአብ ፡ ዘንድ ፡ የሚሰድል ን ፡ጰራቅሊጦስ ፡ አለን ፡ (ጥቅ) ፡ እስእሎ ፡ ለአብ ፡ ይፌኑ ፡ ለክሙ ፡ ጰራቅሊጦስሃ፡ መንፈሰ ፡ ጽድቅ፡ እንዲል ። አንድም ፡ አብ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚሰጠን ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ አለን ፡ ዐሪግየ ፡ ኀበ ፡ አብ ፡ እፌኑ ፡ ለክሙ ፡ ጰራቅሊጦስሃ ፡ ካልአ ፡ እንዲል ። ሐተታ ፡ በወዲያው ፡ አብ ፡ ባይለው ፡ በወዲሁ ፡ አበ ፡ ዓለም ፡ ሐዲስ ፡ ይለዋልና ። አንድም ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፡ (ከአብ ፡ ዘንድ ፡ ቢልም ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ የሚሰጠን ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ አለን ፡ ወኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ አለን ፡ (ጥቅ)፡ ዘያፈቅረኒ፡ ይዐቀብ ፡ ቃልየ ፡ ወያፈቅሮ ፡ አቡየ ፡ አነ ፡ ወአብ ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ንመጽእ ፡ ኀቤሁ ፡ ወንገብር ፡ ምዕራፈ ፡ ውስቴቱ ፡ እስመ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ወኀይሉ ፡ ወመንፈሱ ፡ የዐርፍ ፡ ላዕሌክሙ ፡ እንዲል ። ጰራቅሊጦስ ፡ ማለት ፡ መንጽሒ ፡ መጽንዒ ፡ መስተፍሥሒ ፡ መስተሥርዪ ፡ ከሣቲ ፡ ናዛዚ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፴፬ ። ዕብ ፡ ፯ ፡ ፳፭ ።

፪ ፤ ጻድቅ ፡ ውእቱ ፡ ይኅድግ ፡ ለነ ፡ ኃጣውኢነ ፡

ኃጢአታችንን ፡ ያስተሠርይልን ፡ ዘንድ ፡ ቸር ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡

ወአኮ ፡ በእንቲአነ ፡ ባሕቲቱ ፡

ማስተሥረዩም ፡ የኛን ፡ ብቻ ፡ ኃጢአት ፡ አይደለም ፡

አላ ፡ በእንተ ፡ ዓለምኒ ።

የሰውንም ፡ ሁሉ ፡ ነው ፡ እንጅ ። አንድም ፡ (አኮ ፡ በእንቲአነ) ፡ ኃጢአት ፡ ማስተሥረዩ ፡ በኛ ፡ ብቻ ፡ አድሮ፡ አይደለም፤ እንግዴህም ፡ ወዲህ ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ በሚነሡ ፡ መምህራን፡አድሮ ፡ ያስተሠርያል ፡ እንጅ ፡ ቆላ ፡ ፩ ፡ ፳ ።

፫ ፤ ወበእንተ ፡ ዝ ፡ ንአምር ፡ ከመ ፡ አእመርናሁ ፡ ለእመ ፡ ዐቀብነ ፡ ትእዛዞ ።

ሕጉን ፡ ብንጠብቅ ፡ እንደ ፡ ወደድነው ፡ በዚህ ፡ እናውቃለን ።

፬ ፤ ወዘሰ ፡ ይብል ፡ አአምሮ ፡

እግዚአብሔርን ፡ እወደዋለሁ ፡ የሚል ፡

ወኢየዐቀብ ፡ ትእዛዞ ፡

ትእዛዙን ፡ የማይጠብቅ ፡

ሐሳዊ ፡ ውእቱ ፡

ሐሰተኛ ፡ ነው ፡

ወአልቦ ፡ ጽድቀ ፡ እግዚአብሔር፡ በኀቤሁ ።

በእሱ፡ ዘንድ፡ ዕውነት ፡ የለም። አንድም ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ አላደረበትም ፡ ... ም ፡ ፩ ፡ ፷ና ፡ ፬ ፡ ፳ ።

፭ ፤ ወዘሰ ፡ የዐቅብ ፡ ቃሎ ፡

ሕጉን ፡ የሚጠብቅ ፡ ግን።

አማን ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር። ፍጹም ፡ ላዕሌሁ ።

በዕውነት ፡ ፍጹም ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብ... ሔር ፡ አድሮበታል ፡

ወበዝንቱ ፡ ነአምር ፡ ከመ ፡ ቦቱ፡ ሀለውነ ።

በዚህም ፡ እሱን ፡ በመወደድ። አንድም ... ጌትነቱን ፡ በማመን ፡ እንድንኖር ፡ እናውቃለን ፡ ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፳፩ ፡ ፳፫ ።

፮ ፤ ወዘሰ ፡ ይብል ፡ ቦቱ ፡ ሀሎኩ ፡

እሱን ፡ በመውደድ ፡ እሱን ፡ በማመን፡ ... ንቼ ፡ እኖራለሁ ፡ የሚል።

መፍትው ፡ ይሖር ፡ በከመ ፡ ሖረ፡ ዝክቱ ።

እሱ፡እንደ፡ ኖረ፡ ሊኖር፡እሱ፡ እንደ፡ ሄደ፡ ... ሊሄድ ፡ ይገባዋል ፡ ዮሐ፡ ፲፫ ፡ ፬ ፡ ፫ ።

፯ ፤ አኀዊነ ፡ አኮ ፡ ትእዛዘ ፡ ሐዲሰ ፡ ዘእጽሕፍ ፡ ... ለክሙ ፡

ወንድሞቻችን ፡ እንግዳ፡ ትእዛዝን ፡ የም... ጽፍላችሁ ፡ አይደለም ፡

አላ ፡ ትእዛዘ ፡ ብሊተ ፡ እንተ ፡ብክሙ ፡ ትካት ፡

በጥንተ ፡ ስብከት ፡ የሰማችኋትን ፡ የ... ረች ፡ ሕግን ፡ ነው ፡ እንጅ ። አንድም ፡ ... ትእዛዝ ፡ ሐዲስ ፡ የምጽፍላችሁ ፡ እንግዳ ... ትእዛዝ ፡ አይደለችም ፡ አላ ፡ ትእዛዝ ... ብሊት ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ የሰማችኋት ... ሕግ ፡ ናት ፡ እንጅ ፡

እስመ ፡ ትእዛዝ ፡ ብሉይ ፡ ወእቱ ፡ ዝንቱ ፡ ቃል ... ዘሰማዕክሙ ።

ይህ ፡ የሰማችሁት ፡ ቃል ፡ የኖረ ፡ ሕግ ...



www.ethiopianorthodox.org

ንውና፤ መፍትው፡ ይሑር፡ ላለው፡ እመ ፡
ቦ ፡ ዘይትለዐከኒ ፡ ለይትልወኒ ፡ እስመ ፡
ኀበ ፡ ሀሎኩ ፡ አነ ፡ ሀየ ፡ ይሄሉ ፡ ዘይት
ለዐከኒ ፡ ሲል ፡ የሰማችሁት ፡ ነው፡ እንጅ፡
ወአኮ ፡ በእንቲአነ ፡ ባሕቲቱ ፡ ላለው ፡
አኮ ፡ በእንተ ፡ እሉ ፡ ባሕቲቶሙ ፡ ዘእስ
እለከ ፡ አላ ፡ በእንተሂ ፡ እለ ፡ የአምኑ ፡
ብየ ፡ በቃሎሙ ፡ ሲል ፡ የሰማችሁት ፡
ነው ፡ እንጅ ፡ ለእመ ፡ ዐቀብነ ፡ ትእዛዞ ፡
ላለው ፡ ወእመሰ ፡ ታፈቅሩኒ ፡ ዕቀቡ ፡
ትእዛዝየ ፡ ዘያፈቅረኒ ፡ ይዕቀብ ፡ ቃልየ ፡
ሲል ፡ የሰማችሁት ፡ ነው ፡ እንጅ ።

፰ ፤ ወካዕበ ፡ ትእዛዘ ፡ ሐዲሰ ፡ እጽሕፍ ፡ ለክሙ ፡

ዳግመኛም ፡ እንግዳ ፡ ትእዛዝን። አንድም
እንግዳ ፡ ትእዛዝ ፡ አድርጌ ፡ እጽፍላች
ኋለሁ ፡

ወውእቱ ፡ እሙን ፡ ብክሙ ፡

ይኸውም ፡ በናንተ ፡ ጸንቶ ፡ ይኑር ፡

ወአንትሙኒ ፡ ቦቱ ፡

እናንተም ፡ በሱ ፡ ጸንታችሁ ፡ ኑሩ ፡

እስመ ፡ ኀለፈ ፡ ጽልመት ፡

ድንቁርና። አንድም ፡ አራት ፡ አልፋለችና፤

ወብርሃን ፡ ዘበአማን ፡ ወድአ ፡ አስተርአየ ።

ዕውቀት ፡ ወንጌል፡ ፈጽሞ፡ ተሰጥትዋል
ና ፡ ሮሜ ፡ ፲፫ ፡ ፲፪ ።

፱ ፤ ወዘሰ ፡ ይብል ፡ ውስተ ፡ ብርሃን ፡ ሀሎኩ ፡

ቦቱ ፡ ላለው ፡ በብርሃን ፡ ማለት ፡ በው
ቀት ፡ በወንጌል ፡ እኖራለሁ ፡ የሚል ፡

ወይጸልእ ፡ ቢጾ ፡

ወንድሙን ፡ የሚጠላ ፡

ሐሳዊ ፡ ውእቱ ፡

ሐሰተኛ ፡ ነው ፡

ወውስተ ፡ ጽልመት ፡ ሀሎ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ።

ገና ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በጨለማ ፡ ይኖራል ፡
አለ ፡ በድንቁርና ፡ በአራት ፡ ይኖራል ፡
ም ፡ ፫ ፡ ፲፰ና ፡ ፬ ፡ ፳ ።

፲ ፤ ወዘሰ፡ ያፈቅር፡ ቢጾ፡ ውስተ፡ ብርሃን፡ ይነብር፡

ወንድሙን ፡ የሚወድ ፡ ግን ፡ በዕውቀት ፡
በወንጌል ፡ ይኖራል ፡

ወአልቦ ፡ ዕቅፍት ፡ በኀቤሁ ።

ምግባር፡ ልሥራ፡ ትሩፋት፡ ላብዛ ፡ ቢል ፡
መሰናክል ፡ የለበትም ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፲፬ ።

፲፩ ፤ ወዘሰ ፡ ይጸልእ ፡ ቢጾ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡
የሐውር ፡

ወንድሙን ፡ የሚጠላ ፡ ግን ፡ በድንቁርና፡
በአራት ፡ ይኖራል ፡

ወኢየአምር ፡ ኀበ ፡ የሐውር ፡

የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ አያውቀውም ፡

እስመ ፡ ጽልመት ፡ አዖሮ ፡ አዕይንቲሁ ።

ድንቁርና ፡ እንዳያውቅ ፡ አድርጎታልና ።
አንድም ፡ (ወዘሰ ፡ ያፈቅር ፡ ቢጾ ፡ )ወን
ድሙን ፡ የሚወድ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማይ፡
ይኖራል ። (ወአልቦ ፡ ዕቅፍት) ፡ ዕቅፍተ ፡
ነፍስ ፡ የለበትም ። (ወዘሰ ፡ ይጸልእ) ፡ ወን
ድሙን ፡ የሚጠላ ፡ ግን ፡ በገሃነም ፡ ይኖ
ራል ፤ (ወኢየአምር) ፡ የሚሄድበትንም ፡
አያውቀውም ፡ (እስመ ፡ ጽልመት) ፡ ጨ
ለማ ፡ እንዳያይ ፡ አድርጎታልና ፡ (ጥቅ) ፡
ኢንሬእዮሙ ፡ ለእሙንቱ ፡ ወእሙንቱ ፡
ኢይሬእዩነ ፡ እስመ ፡ ጽልመት ፡ ሀሎ ፡
ማዕከሌነ ፡ ወኢየኀድገነ ፡ ንትረአይ ፡ በበ
ይናቲነ ፡ ወይመስለነ፡ ከመ፡ ዘባሕቲትነ ፡
ሀሎነ ፡ እንዘ ፡ ብዙኀ ፡ ጉባኤ ፡ ሀሎ ፡ ምስ
ሌነ ፡ እንዲል ።

፲፪ ፤ እጽሕፍ ፡ ለክሙ ፡ ደቂቅየ ፡

ልጆቼ ፡ እጽፍላችኋለሁ ፡



እስመ ፡ ተኀድገ ፡ ለክሙ ፡ ኃጢአትክሙ ፡ በእንተ ፡
ስሙ ።

በስሙ ፡ ስላመናችሁ ፡ በስሙ ፡ ስለ ፡ ተጠ
ራችሁ ፡ ስሙን ፡ ስላስተማራችሁ ፡ ኃጢ
አታችሁ ፡ ተሠርዮላችኋልና ። ተሠርዮ
ላችኋል ፡ ብዬ ፡ እንደ ፡ ተሠረየላችሁ ፡
ሳጠይቅ፡ ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፵፯። የሐዋ ፡ ፬፡ ፲፪።

፲፫ ፤ እጽሕፍ ፡ ለክሙ ፡ አበው ፡

አበው ፡ እጽፍላችኋለሁ ፡

እስመ ፡ አእመርክምዎ ፡ ለቀዳማዊ ፡

ሙቶ ፡ የተነሣው ፡ ቀዳማዊ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
አውቃችሁታልና ። አንድም ፡ አውቃች
ሁታል ፡ ብዬ ፡ እንዳወቃችሁት ፡ ሳጠ
ይቅ ፡

እጽሕፍ ፡ ለክሙ ፡ ወራዙት ፡

ወራዙት ፡ እጽፍላችኋለሁ ፡

እስመ ፡ ሞእክምዎ ፡ ለእኩይ ፡

እኩይ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋን ። አንድም ፡ እኩ
ይ ፡ ፈቃደ ፡ ሰይጣንን ፡ ድል ፡ ነሥታ
ችሁታልና ። አንድም ፡ ድል ፡ ነሥታችሁ
ታል ፡ ብዬ ፡ ድል፡ እንደነሣችሁት ፡ ሳጠ
ይቅ ፡

ጸሐፍኩ ፡ ለክሙ ፡ ደቂቅየ ፡

እንደ ፡ ገናን ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ
ም ፡ ቀደም ፡ ጻፍሁላችሁ ፡

እስመ ፡ አእመርክምዎ ፡ ለአብ ።

አብን ፡ አውቃችሁታልና ፡ አውቃችሁ
ታል ፡ ብዬ ፡ እንዳወቃችሁት ፡ ሳጠይቅ ።

፲፬ ፤ ጸሐፍኩ ፡ ለክሙ ፡ አበው ፡ እስመ ፡ አእመር
ክምዎ ፡ ለቀዳማዊ ፡

ቀዳማዊ ፡ አብን ፡ አውቃችሁታልና ፡

ጸሐፍኩ ፡ ለክሙ ፡ ወራዙት ፡ እስመ ፡ ጽኑዓን ፡ አን
ትሙ ፡

ድል ፡ ነሥታችኋልና ፡

ወቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይነብር ፡ ኀቤክሙ ፡

ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወንጌልም ፡ በናን
ተ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራልና ፡

ወሞእክምዎ ፡ ለእኩይ ።

እኩይ፡ፈቃደ፡ሥጋን፡እኩይ፡ፈቃደ፡ ሰይጣ
ንን፡ድል፡ ነሥታችኋልና።አንድም ፡ እካ
ላዊ ፡ ቃል ፡ በናንተ ፡ አድሮ ፡ ይኖራልና ፡
ይነብር ፡ ላለው ። ሐተታ ፡ እሊህ ፡ ሁሉ ፡
ባንድ ፡ አገር ፡ ይኖራሉና ፡ እሊህን ፡ ሁሉ፡
አንድ ፡ ሰው ፡ ይረግጣቸዋልና ፡ ንጹሐን ፡
ናቸውና ፡ ሕፃናት ፡ አላቸው ፡ (ጥቅ) ፡
ንጽሐሙ ፡ ለሕፃናት ፡ በሥጋሆሙ ፡ እም
ንእሰሙ ፡ ከመ ፡ መላእክተ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ እንዲል ። ድል ፡ ነሥተዋልና ፡ ወራ
ዙት ፡ አዋቆች ፡ ናቸውና ፡ አበው ፡ አላ
ቸው ፡ (ፍጹማን ፡ ናቸውና ፡ ቢል ፡ ይሆ
ናል) ፡ ኤፌ ፡ ፯ ፡ ፲ ።

፲፭ ፤ ኢታፍቅርዎ ፡ ለዓለም ፡

ይህን ፡ ዓለም ፡ አትውደዱ ፡

ወኢዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡

በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለውን ፡ ቤቱን ፡ ንብረ
ቱን ፡ አትውደዱ ፡

ወዘሰ ፡ አፍቀሮ ፡ ለዓለም ፡

ይህን ፡ ዓለም ፡ የወደደ ፡

ኢሀሎ ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕሌሁ ።

ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ አላደረበትም ፡
ማለት ፡ ጌታ ፡ በወንጌል ፡ ምንት ፡ ይበ
ቍዖ ፡ ለሰብእ ፡ ለእመ ፡ ኵሎ ፡ ዓለመ ፡
ረብሐ ፡ ወነፍሶ ፡ ሐጕለ ፡ ያለውን ፡ አል
ያዘም ፡ ያዕ ፡ ፬ ፡ ፬ ። አንድም ፡(ኢታፍቅ
ርዎ ፡ ከተማን)፡ አትውደዱ፡ (ወኢዘሀሎ)፡
በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ሹመት ፡
ሽልማት ፡ አትውደዱ ። (ወዘሰ ፡ አፍ
ቀሮ) ፡ ከተማን፡ የወደደ፡ (ኢሀሎ) ፡ ጌታ ፡

www.ethiopianorthodox.org

በጳውሎስ ፡ አድሮ ፡ ንፃእ ፡ አፍአ ፡ እም ትዕይንት ፡ ያለውን ፡ አልያዘም ። አን ድም ፡ (ኢታፍቅርዎ) ፡ እናት ፡ አባታች ሁን ፡ አትውደዱ ። (ወኢዘሀሎ) ፡ በናት ፡ ባባታችሁ ፡ ያለውን ፡ ርስት ፡ ጉልት ፡ አትውደዱ ፡ (ወዘሰ) ፡ እናት ፡ አባቱን ፡ የወደደ ፡ (ኢሀሎ) ፡ ጌታ ፡ በወንጌል ፡ ዘኢ ኀደገ ፡ አባሁ ፡ ወእሞ ፡ ቤቶ ፡ ወውሉዶ ፡ ኢይክል ፡ ይፀመደኒ ፡ ያለውን ፡ አልያ ዘም ። አንድም ፡ (ኢታፍቅርዎ) ፡ ሥጋች ሁን ፡ አትውደዱ ። (ወኢዘሀሎ) ፡ በሥጋ ችሁ ፡ ያለውን ፡ መብል ፡ መጠጥ ፡ አት ውደዱ ፡ አለ ። ከሳ ፡ እናወፍረው ፡ ጠቈረ፡ እናቅላው ፡ አትበሉ ። (ወዘሰ ፡ አፍቀሮ) ፡ ሥጋውን ፡ የወደደ ፡ (ኢሀሎ) ፡ ጌታ ፡ በጳ ውሎስ ፡ አድሮ ፡ እስመ ፡ ሐሊናሁ ፡ ለነ ፍስትነ ፡ ፀሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያለውን ፡ አልያዘም ። (ኢትፍርህዎሙኬ ፡ ለእለ ፡ ይቀትሉ ፡ ሥጋክሙ ፡ የሚሉ ፡ አሉ ። አን ድም ፡ (ኢታፍቅርዎ) ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ አትውደዱ ። (ወኢዘሀሎ) ፡ በውስጡ ፡ ያ ለውን ፡ ሥራይ ፡ ማብላት ፡ መርዝ ፡ ማጠ ጣትን ፡ አትውደዱ ። (ወዘሰ ፡ አፍቀሮ) ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ የወደደ ፡ (ኢሀሎ) ፡ ጌታ ፡ በወንጌል ፡ ኢታጥርዩ ፡ ወርቀ ፡ ወብሩረ ፡ ያለውን ፡ አልያዘም ። ታሪክ ፡ እንደ ፡ ሁለት ፡ አኀው ፡ ሁሉም ፡ በበረሃ ፡ ይኖ ራሉ ፡ ይዋደዳሉ ፡ አንዱ ፡ ለተልእኮ ፡ ሲወጣ ፡ አንዱ ፡ ከቤት ፡ የቀረው ፡ ዛሬ ፡ ወንድሜን ፡ ምን ፡ አግኝቶት ፡ ይሆን ፡ እ ያለ ፡ ይጨነቃል ፡ አንዱም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ አንዱ ፡ እንደዚያው ፡ ይጨነቃል ፡ ሰይጣን ፡ በመካከል ፡ ድስት ፡ ሙሉ ፡ ወ ርቅ ፡ አስገኘ ፡ አንዱ ፡ ወንድሜ ፡ ሙቶ ልኝ ፡ ይህን ፡ ወርቅ ፡ ይዤ ፡ ከተማ ፡ ገብ ቼ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አድርጌ ፡ እያለ ፡ ይ መኘ ፡ ገ'መረ ፡ አንዱም ፡ እንደዚያው ፡ ያስብ ፡ ጀመረ ፡ ከመካከል ፡ አንዱን ፡ ኮሶ ፡ ታየው ፡ ወንድሜ ፡ ኮሶ ፡ ታይቶኛ ልና ፡ ደቁስህ ፡ አጠጣኝ ፡ አለው ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ መርዝ ፡ ጨምሮ ፡ በጥብጦ ፡ ደርሶ ልሃልና፡ ና ፡ ጠጣ፡ አለው ያም፡ ሰይፉን ፡ ሲስል ፡ ቆይቷል ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ሰይፉን ፡ በልብሱ ፡ ሰውሮ ፡ ይዞ ፡ መጣ ፡ አንሥ ተህ ፡ ጠጣ ፡ አለው ፡ አንተ ፡ አንሥተህ ፡ ስጠኝ ፡ አለው ፡ አንሥቼ ፡ እሰጠዋለሁ ፡ ሲል ፡ በዚያ ፡ ሰይፍ ፡ አንገቱን ፡ ቀልቶ ፡ ጣለው ። እንግዴህ ፡ ኮሶዬን ፡ ጠጥቼ ፡ ሽሬ ፡ ወርቁን ፡ ይዤ ፡ ከተማ ፡ ገብቼ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አድርጌ ፡ እኖራለሁ ፡ ብሎ ፡ አንሥቶ ፡ ቢጠጣው ፡ ያም ፡ ከዚያ ፡ ያም ፡ ከዚያ ፡ ወድቀዋል ፡ ወርቅ ፡ በመ ካከል ፡ ቀርቷል ።

፲፮ ፤ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ፍት ወቱ ፡ ለሥጋ ፡

በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ የሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ ነውና ፡

ወፍትወቱ ፡ ለዐይን ፡

የዐይን ፡ አምሮት ፡ ነውና ፡

ወስራሑ ፡ ለመንበርት ፡

የዚህ ፡ ዓለም ፡ አነዋወር ፡ ድካም ፡ ነውና፤

ኢኮነ ፡ ዝንቱ ፡ እምኀበ ፡ አብ ፡

ይህ ፡ ከአብ ፡ የተገኘ ፡ አይደለምና ።

አላ ፡ እምዓለም ፡ ውእቱ ።

ከሰይጣን ፡ የተገኘ ፡ ነው ፡ እንጅ ።

ኢታፍቅርዎ ፡ ላለው ። አንድም ፡ የሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ የዐይን ፡ አምሮት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ከሰይጣን ፡ የተገኘ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘ ፡ አይደለ ምና ፡ ኢታፍቅርዎ ፡ ላለው ። አንድም ፡



በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ የሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ ነውና ፡ የዐይን ፡ አምሮት ፡ ነው ና ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ አነዋወር ፡ ድካም ፡ ነው ና ፡ ይህ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘ ፡ አይ ደለም ፡ ከሰይጣን፡ የተገኘ ፡ ነው ፡ እንጅ።

፲፯ ፤ ዓለሙኒ ፡ የኀልፍ ፡

ዓለሙ ፡ ያልፋል ፡

ወፍትወቱኒ ፡ ይኀልፍ ፡

ፈቃዱም ፡ ያልፋል ፡

ወዘሰ ፡ ይገብር ፡ ፍትወቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይነ ብር ፡ ለዓለም ፡

እግዚአብሔር ፡ የሚወደውን ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ ግን ፡ ባለማለፍ ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ።

፲፰ ፤ ደቂቅየ ፡ ዛቲ ፡ ሰዓት ፡ ደኃሪት ፡ ይእቲ ፡

ልጆቼ ፡ ይህች ፡ ሰዓት ፡ የኋላ ፡ ሰዓት ፡ የኋላ ፡ ሰዓት ፡ ይህች ፡ ሰዓት ፡ ናት ። አን ድም ፡ የዛሬ ፡ ሰዓት ፡ የኋላ ፡ ሰዓት ፡ የኋላ፡ ሰዓት ፡ የዛሬ ፡ ሰዓት ፡ ናት ፡

ወበከመ ፡ ሰማዕክሙ ፡ ከመ ፡ ይመጽእ ፡ ሐሳዌ ፡ መሲሕ ፡

መሲሕ ፡ ክርስቶስን ፡ የሚያሳብል ። አን ድም ፡ በመሢሕ ፡ በክርስቶስ፡ የሚያብል፡ ሐሳዊ ፡ መሢሕ ፡ እንዲነሣ ፡ ቀድሞ ፡ እንደሰማችሁ ፡

ወይእዜኒ ፡ ኮኑ ፡ ብዙኃን ፡ ሐሳውያን ፡ መሢሕ ፡

ዛሬም ፡ በመሢሕ ፡ በክርስቶስ ፡ የሚያ ብሉ ። አንድም ፡ መሢሕ ፡ ክርስቶስን ፡ የሚያሳብሉ ፡ ብዙ ፡ ሐሰተኞች ፡ መም ህራን ፡ ተነሥተዋል ፡

ወበዝንቱ ፡ አእመርነ ፡ ከመ ፡ ደኃሪት፡ ሰዓት፡ ይእቲ።

በዚህም ፡ ይህች ፡ ሰዓት ፡ የኋላ ፡ ሰዓት ፡ የኋላ ፡ ሰዓት ፡ ይህች ፡ ሰዓት ። አንድም ፡ የዛሬ ፡ ሰዓት ፡ የኋላ ፡ ሰዓት ፡ የኋላ ፡ ሰዓ ት ፡ የዛሬ ፡ ሰዓት ፡ እንደ፡ ሆነች፡ አወቅን ፡ ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፳ ፡ ፳፬ ።

፲፱ ፤ እስመ ፡ እምኔነ ፡ ወፅኡ ፡ እለ ፡ ኢኮኑ ፡ ባ ሕቲቶ ፡ እምኔነ ፡

በሃይማኖት፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ያልሆኑ፡ ሰዎች ፡ በአማርኛ ፡ ከኛ ፡ ተለይተዋልና ፡

ወሶበሰ ፡ እምኔነ ፡ እሙንቱ ፡ እምነበሩ ፡ ምስሌነ ።

በሃይማኖት፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ ቢሆንስ ፡ ባማርኛ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ በሆኑ ፡ ነበር ።

ወባሕቱ ፡ ከመ ፡ ይትዐወቁ ፡ ከመ ፡ ኢኮኑ ፡ ኵሎሙ ፡ እምኔነ ።

በሃይማኖት ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ያል ሆኑ ፡ እሊህ ፡ በሃይማኖት ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እንዳልሆኑ ፡ ይታወቁ ፡ ዘንድ ፡ ባማርኛ ፡ ተለይተዋል ፡ እንጅ ። ወአንት ሙሰ ፡ ማንሻ ። አንድም ፡ (እስመ ፡ እም ኔነ) ፡ በሃይማኖት ፡ ባማርኛ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ያልሆኑ ፡ እሊህ ፡ በልጅነት ፡ በ ቦታ ፡ ከኛ ፡ ተለይተዋልና ፡ (ደኃሪት ፡ ሰዓት ፡ ይእቲ ፡ ላለው) ፡ በሃይማኖት ፡ ባማርኛስ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ ቢሆን ፡ በልጅነት ፡ በቦታ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ በሆኑ ፡ ነበር ፤ በሃይማኖት ፡ ባማ ርኛ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ያልሆኑ ፡ እሊህ በልጅነት ፡ በቦታ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እንዳይደሉ ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ የሐዋ ፡ ፳ ፡ ፴ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፱ ።

፳ ፤ ወአንትሙሰ ፡ ቅብዓት ፡ ብክሙ ፡ እምነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡

ለናንተስ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ፡ የተቀበላች ሁት፡ዕውቀት፡ አንድም፡ ልጅነት፡አላችሁ፡

ወተአምሩ ፡ ኵሎ ።

ዕውቀትን ፡ ልጅነትን ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱ ስ ፡ ገንዘብ ፡ አድርጋችሁ ፡ ሁሉን ፡ ታው ቃላችሁ ፡ ቍ ፡ ፳፯ ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፩ ፤ ኢጸሐፍኩ ፡ ለክሙ ፡ ከመ ፡ ዘኢተአምርዋ ፡ ለጽድቅ ፡

ወንጌልን ፡ ሃይማኖትን ፡ እንደማታውቋት ፡ አድርጌ ፡ አታውቋትም ፡ ብዬ ፡ እንዳታውቋት ፡ ሳጠይቅ ፡ አልጻፍሁላችሁም ፡

አላ ፡ ከመ ፡ ተአምርዋ ፡

ታውቋታላችሁና ፡ ታውቋታላችሁ ፡ ብዬ፡ እንድታውቋት ፡ ሳጠይቅ ፡ ጻፍሁላችሁ ፡ እንጅ ፡

እስመ ፡ ኵሉ ፡ ሐሰት ፡ ኢኮነት ፡ እምጽድቅ ።

ሐሰት ፡ ሁሉ ፡ ከጽድቅ ፡ ወገን ፡ አይደለችምና ።

፳፪ ፤ ወመኑ ፡ ውእቱ ፡ ሐሳዊ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘይክሕድ ፡ ወይብል ፡ እስመ ፡ ኢየሱስ ፡ ኢኮነ ፡ መሢሐ ፡

ኢየሱስ ፡ መሢሕ ፡ አይደለም ፡ ከሚል ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ነው ፡ እንጅ፤ ያለሱ ፡ ሐሰተኛ ፡ ማነው ። አንድም ፡ ኅድረት ፡ ከሚል ፡ ከንስጥሮስ ፡ በቀር ፡ ሐሰተኛ ፡ ማነው ፡ የለም ። ሐተታ ፡ ምነው ፡ ሥጋ ፡ አምላክ ፡ አይደለም ፡ ብኋል ፡ እንጅ ። ቃል ፡ መሢሕ ፡ አይደለም ፡ ብኋልና ፡ እንዲሀ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ ቃልንስ ፡ መሢሕ ፡ ብሎ ፡ ቢሆን ፡ ሥጋን ፡ አምላክ ፡ ባለ ፡ ነበር ፡ ቀንኛ ፡ ተዋሕዶን ፡ አለ ፡

ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ሐሣዌ ፡ መሢሕ ፡

መሢሕ ፡ ክርስቶስን ፡ የሚያሳብል ፡ በመሢሕ ፡ በክርስቶስ ፡ የሚያብል ፡ ሐሰተኛ ፡ መሢሕ ፡ ይሀ ፡ ነው ፡

ዘይክሕድ ፡ በአብ ፡ ወበወልድ ።

አብን ፡ ወላዲ ፡ ወልድን ፡ ተወላዲ ፡ ብሎ፡ የማያምን ።

፳፫ ፤ ወኵሉ ፡ ዘይክሕድ ፡ በወልድ ፡ ወበአብኒ ፡ ኢሀለወ ፡

ወልድን ፡ ተወላዲ ፡ ብሎ ፡ የማያምን ፡ አብን ፡ ወላዲ ፡ ብሎ ፡ በማመን ። አንድም ፡ ወልድን ፡ ዓለም ፡ ቦታ ፡ በማድረግ ፡ የማይኖር ፡ አብን ፡ ዓለም ፡ ቦታ ፡ በማድረግ ፡ አይኖርም ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እንዳለች ፡ አያምንም ፡

ወዘሰ ፡ የአምን ፡ በወልድ ፡ ወበአብኒ ፡ ሀለወ ።

ወልድን ፡ ተወላዲ ፡ ብሎ ፡ በማመን ። አንድም ፡ ዓለም ፡ ቦታ ፡ በማድረግ ፡ የሚኖር ፡ አብን ፡ ወላዲ ፡ ብሎ ፡ በማመኒ ። አንድም ፡ ዓለም ፡ ቦታ ፡ በማድረግ ፡ ይኖራል ፡ መንግሥት ፡ ሰማይ ፡ እንዳለች ፡ ያምናል ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፲፭ ።

፳፬ ፤ ወአንትሙሰ ፡ ዘሰማዕክሙ ፡ ትካት ፡ ለይንበር ፡ ኀቤክሙ ፡

እናንተስ ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ የሰማችሁት ፡ ትምህርት ፡ በናንት ፡ ጸንቶ ፡ ይኑር፡

ወእመሰ ፡ ዘሰማዕክሙ ፡ ትካት ፡ ነበረ ፡ ኀቤክሙ ፡

በጥንተ ፡ ስብከት ፡ የሰማችሁትስ ፡ ትምህርት ፡ በናንት ፡ ጸንቶ ፡ ካለ ፡ (ከኖረ) ፡

ወአንትሙኒ ፡ ትነብሩ ፡ በአብ ፡ ወበወልድ ።

እናንተም ፡ አብን ፡ ወላዲ ፡ ወልድን ፡ ተወላዲ ፡ ብላችሁ ፡ በማመን ። አንድም ፡ አብን ፡ ዓለም ፡ ቦታ ፡ ወልድን ፡ ዓለም ፡ ቦታ ፡ በማድረግ ፡ ትኖራላችሁ ፡ መንግሥት ፡ ሰማይ ፡ እንዳለች ፡ ታምናላሁች ።

፳፭ ፤ ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ተስፋ ፡ እንተ ፡ አሰፈወነ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡

የዘለዓለም ፡ ድኅነትን ፡ እንድናገኝባት ፡ የነገረን ፡ ሃይማኖት ፡ ይህች ፡ ናት ፡ አለ ፤ አብን ፡ ወላዲ ፡ ወልድን ፡ ተወላዲ ፡ ብሎ ፡ ማመን ። አንድም፡ የዘለዓለም ፡ ድኅነትን ፡ እንድናገኝባት ፡ የነገረን ፡ ተስፋ ፡ ይህች ፡ ናት፡ አለ ፡ አብን ፡ ዓለም ፡ ቦታ ፡ ወልድን ፡ ዓለም ፡ ቦታ ፡ አድርጎ ፡ መኖር፡ መንግሥት ፡ ሰማይ ፡ እንዳለች ፡ ማመን ።



፳፮ ፤ ወዘንተ ፡ ንጽሕፍ ፡ ለክሙ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ያስሕቱክሙ ።

ሲናገረው፡ የመጣውን፡ ዘንተ፡ አለ፡ ስለሚያስቷችሁ፡ሰዎች፡ይህን፡እንጽፍላችኋለን ።

፳፯ ፤ ወአንትሙሰ ፡ ቅብዓት ፡ ብክሙ ፡ እንተ ፡ ነሣእክሙ ፡ እምኀቤሁ ፡

እናንተስ ፡ ከሱ ፡ የተቀበላችሁት ፡ ዕውቀት ። አንድም ፡ ልጅነት ፡ አላችሁ ፡

ትነብር ፡ ኀቤክሙ ፡

በናንት ፡ ትኖር ፡ ዘንድ ፡ ትንበር ፡ በናንት ፡ ጸንታ ፡ ትኑር ። አንድም ፡ በናንት ፡ ጸንታ ፡ ትኖራለች ፡

ወኢትፈቅዱ ፡ መኑሂ ፡ ይምሀርክሙ ፡

ማንም ፡ ማን ፡ ሊያስተምራችሁ ፡ አትሹም ፡ (ኢትፍቅዱ ፡ መነሂ) ፡ ማነንም ፡ ማነን ፡ አትሹ ፡

አላ ፡ መንፈስ ፡ ዚአሁ ፡ ይሜህረክሙ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ

የባሕርይ ፡ ሕይወቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሁሉን ፡ ይገልጽላችኋል ፡ እንጅ ፡

ወእሙን ፡ ውእቱ ፡

የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መምህርነቱ ። አንድም ፡ ትምህርቱ ፡ የታመነ ፡ ነው ፡

ወኢኮነ ፡ ሐሰተ ።

ሐሰት ፡ አይደለም ፡ ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፳፮ና ፡ ፲፯ ፡ ፲፫ ።

፳፰ ፤ ወበከመ ፡ ትምህርትክሙ ፡ ንበሩ ፡ ባቲ ፡ ወይእዜኒ ፡ ደቂቅየ ፡ ንበሩ ፡ ባቲ ፡

ንበሩ ፡ ባቲና ፡ ንበሩ ፡ ባቲ ፡ አንድ ፡ ወገን፡ በተማራችኋት፡ ትምህርት፡ጸንታችሁ፡ኑሩ፡

ከመ ፡ አመ ፡ አስተርአየ ፡ ንርከብ ፡ ገጸ ፡ በዕለተ ፡ ደይን ፡

በጌትነት ፡ በተገለጸ ፡ ጊዜ ፡ በቍርፀ ፡ ፍርድ፡ቀን፡ባለሟልነትን፡እናገኝ፡ ዘንድ ።

ወኢንትሐፈር ፡ እምኔሁ ፡ አመ ፡ ይመጽእ ።

በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ከሱ ፡ ክብር ፡ እንዳናጣ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፳፩ ።

፳፱ ፤ ወእመሰ ፡ ርኢክሙ ፡ ከመ ፡ ጻድቅ ፡ ውእቱ ፡

መምህርነቱ ። አንድም ፡ ትምህርቱ ፡ ዕውነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ። አንድም ፡ ጌታ ፡ ቸር ፡ የባሕርይ፡አምላክ፡እንደ፡ሆነ፡ካወቃችሁስ፡

አእምሩ ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ዘይገብራ ፡ ለጽድቅ ፡ እምኔሁ ፡ ተወልደ ።

ጽድቅን ፡ የሚሠራት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከሱ ፡ የተማረ ፡ ከሱ ፡ የተወለደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕወቁ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፯ ፡ ፲ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩ ፤ ወርእዩ ፡ ዘከመ ፡ እፎ ፡ ፍቅሩ ፡ ዘወሀበነ ፡ አብ ፡

አብ ፡ ወልድ ፡ ነው ፡ እኛን ፡ ያፈቀረበት ፡ ፍቅሩ ፡ እንደምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አለ ፡ ደግ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕወቁ ፡

ከመ ፡ ውሉደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንኩን ፡

የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ እንሆን ፡ ዘንድ፤

ወኮነኒ ፡

እንደ ፡ ገናን ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህም ፡ ቀደም ፡ ሁነናል ፡

ወበእንተ ፡ ዝ ፡ ኢፈተወነ ፡ ዓለም ፡

ስለዚህም ፡ ዓለሙ ፡ አልወደደንም ፡

እስመ ፡ ሎቱኒ ፡ ኢያእመሮ ።

እሱን ፡ አልወደደውምና ። አንድም ፡ (ኢፈተውነ ፡ ዓለመ) ፡ ዓለሙን ፡ አልወደድነውም ፡ እሱ ፡ ዓለሙን፡ አልወደደውምና፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ። ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፫ ።

፪ ፤ አኃዊነ፡ ይእዜሰ፡ ደቂቀ፡ እግዚአብሔር፡ ንሕነ፡

ወንድሞቻችን ፡ እንግዲህስ ፡ ወዲህ ፡ በሃ

www.ethiopianorthodox.org

ይማኖት ፡ በጥምቀት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ሆነናል ፡

ወዓዲ ፡ ኢተዐውቀ ፡ ለነ ፡ ምንተ ፡ ንከውን ፡

ምንም ፡ እንድንሆን ፡ ገና ፡ በምግባር ፡ አልታወቀልንም ፡ እንጅ ፡ እንከደውም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አንከደውም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡

ንአምር ፡ ባሕቱ ፡ ከመ ፡ እምከመ ፡ ተዐውቀ ፡ ለነ ፡ ከማሁ ፡ ንከውን ፡

በምግባር ፡ እንዳንከደው ፡ ከታወቀልን ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ልጆቹ ፡ እንድንሆን ፡ እና ውቃለን ፡

እስመ ፡ ንሬእዮ ፡ ሎቱ ፡ በከመ ፡ ውእቱ ።

እሱ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ እንደመሆኑ ፡ እናየዋለንና ። አንድም ፡ (አኀዊነ) ፡ በሃይ ማኖት ፡ በምግባር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ል ጆች ፡ ሆነናል ፤ ኋላ ፡ ምን ፡ እንድንሆን፡ አለ ፡ ንዑ ፡ ይለንም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሑሩ ፡ ይለንም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገና ፡ አልታወቀል ንም ፡ እንጅ ። ንዑ ፡ እንዲለን ፡ ከታወ ቀልን ፡ በኋላ ፡ ግን፡ እሱ ፡ እንደ ፡ መሆኑ፡ እናውቃለን ፤ በትንሣኤ ፡ በርእይ ፡ ፍጥ ረታዊ ፡ በግርማ ፡ መንግሥት ፡ እናይዋለ ንና ፡ (ጥቅ) ፡ ፍጥረትኒ ፡ ትሬእዮ ፡ ለፈጣ ሪሃ ፡ ከዊኖ ፡ በአካለ ፡ ቆማ ፡ እንዲል ፡ ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፲፯ ። ቆላ ፡ ፫ ፡ ፬ ።

፫ ፤ ወኵሉ ፡ ዘተወከለ ፡ ኪያሁ ፡ ያነጽሕ ፡ ርእሶ ፡ በከመ ፡ ውእቱ ፡ ንጹሕ ።

በሱ ፡ ያመነ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እሱ ፡ ንጹሕ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሰውነቱን ፡ ከኃጢአት ፡ ንጹሕ ፡ ያደርጋል ፡ ያንጽሕ ፡ ንጹሕ ፡ ያ ድርግ ።

፬ ፤ ወኵሉ ፡ ዘይገብራ ፡ ለኃጢአት ፡ ወለአበሳኒ ፡ ገብራ ፡ ውእቱ ፡

ጥቃቅኑን ፡ ኃጢአት ፡ የሠራ ፡ ደጋጉን ፡ ኃጢአት ፡ ሠራ ፡

እስመ ፡ ኃጢአት ፡ አበሳ ፡ ይእቲ ።

ጥቃቅኑ ፡ ከደጋጉ ፡ ያደርሳልና ። (ጥቅ) ፡ ተዐቀብ ፡ እምንኡሳት ፡ ኃጣውእ ፡ ከመ ፡ ኢትደቅ ፡ ውስተ ፡ ዐቢያት ፡ እንዲል ። አንድም ፡ ጥቃቅኑ ፡ ከደጋጉ ፡ ጋራ ፡ ከመ ንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ በማውጣት ፡ አንድ ፡ ናቸውና ፡ (ጥቅ) ፡ እላ ፡ ንኡሳት ፡ ኢኮና ፡ ንኡሳተ ፡ አላ ፡ ዐቢያት ፡ ጥቀ ፡ እስመ ፡ እማንቱ ፡ ያርኅቃ ፡ እመንግሥተ ፡ እግዚ አብሔር ፡ እንዲል ። ሽንኩርት ፡ አንድ ፡ ራስም ፡ በሉ ፡ ሁለት ፡ ራስም ፡ በሉ ፡ ሽታው ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ። አንድም ፡ (ወኵሉ ፡ ዘይገብራ) ፡ ኃጢአትን ፡ የሠራ ፡ ክህደትን ፡ ሠራ ፡ ኃጢአት ፡ ክህደት ፡ ናትና፡ (ጥቅ) ፡ እመ፡ ቦ ፡ ዘየአምን፡ ወምግ ባሩ ፡ እኩይ ፡ ውእቱ ፡ ክህደ ፡ ሃይማኖቶ ፡ ወየአኪ ፡ እምዘኢየአምን ፡ እንዲል ።

፭ ፤ ወተአምሩ ፡ ከመ ፡ አስተርአየ ፡ ዝክቱ ፡

ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ተገለጸ ፡ ታው ቃላችሁ ፡

ከመ ፡ ያሰስል ፡ ለኃጢአት ፡

ኃጢአትን ፡ ያጠፋት ፡ ዘንድ ፡

ወኃጢአትሰ ፡ አልቦ ፡ ኀቤሁ ፡

ያሰስላ ፡ ማለቱ፡ ከራሱን ፡ ነው፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በእሱስ ፡ ኃጢአት ፡ የለበ ትም ፤ ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፬ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፳፬ ።

፮ ፤ ወኵሉ ፡ ዘቦቱ ፡ ይነብር ፡ ኢይኤብስ ፡

በእሱም ፡ አምኖ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ አይ በድልም ። ሐተታ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢበ ድል ፡ ሁለተኛ ፡ በሥጋ ፡ ቢበድል ፡ በ ነፍስ ፡ በሐልዮ ፡ ቢበድል ፡ በነቢብ ፡ በ ገቢር ፡ አይበድልም፡ በንስሓ ፡ በፍጹሙ ፡ ተገብቶ ፡

እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘይኤብስ ፡ ኢይሬእዮ ፡ ወኢየአምሮ ።

የሚበድል ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔ ርን፡ አያየውም፡አያውቀውምና።አንድም፡ አያምነውም፡ አይወደውምና፡ሮሜ፡፯፡፲፬።

፯ ፤ ደቂቅየ ፡ ኢያስሕቱክሙ ፡

ልጆቼ ፡ ጥቃቅኑ ፡ ኃጢአት ፡ ከደጋጉ ፡ ኃጢአት ፡ አያደርስም ፤ ጥቃቅኑ ፡ ከደ ጋጉ ፡ ኃጢአት ፡ ጋራ ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰ ማይ ፡ በማውጣት ፡ አንድ ፡ አይደለም ። አንድም ፡ ኃጢአት ፡ ክህደት ፡ አይደላ ትም ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ አያስቷችሁ ፡

ኵሉ ፡ ዘይገብራ ፡ ለጽድቅ ፡ ጻድቅ ፡ ውእቱ ፡ በከመ ፡ ዝክቱ ፡ ጻድቅ ።

ጽድቅን ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እሱ ፡ ጻድቅ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ዕውነተኛ፡ ነው፡ ም ፡ ፪ ፡ ፳፱ ።

፰ ፤ ወዘሰ ፡ ይገብራ ፡ ለኃጢአት ፡ እምነ ፡ ጋኔን ፡ ውእቱ ፡

ኃጢአትን ፡ የሚሠራ ፡ ግን ፡ ከጋኔን ፡ የተ ማረ ፡ ከጋኔን ፡ የተወለደ ፡ ነው ። ጋኔን ፡ ማለት ፡ ዕሩቅ ፡ ውዱቅ ፡ ማለት ፡ ነው ፡

እስመ ፡ ቀዳሚሁ ፡ ሰይጣን ፡ አበሰ ፡

አስቀድሞ ፡ የበደለ ፡ ሰይጣን ፡ ነውና ። ሰይጣን ፡ ማለት ፡ መስተቃርን ፡ መስተ ጻርር ፡ ባላጋራ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ጥቅ) ፡ ወአቀመ ፡ አዴርሃ ፡ ሰይጣነ ፡ ላዕለ ፡ ሰሎ ሞን ፡ እንዲል ፡

ወበእንተ፡ ዝንቱ፡ አስተርአየ፡ ወልደ፡ እግዚአብሔር፡

ስለዚህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ በሥጋ ፡ ተገለጸ ፡

ከመ ፡ ይስዐር ፡ ግብሮ ፡ ለጋኔን ።

የጋኔን፡ግብሩን፡ያጠፋ፡ዘንድ፡ዮሐ፡፰፡፵፩።

፱ ፤ ወኵሉ ፡ ዘይትወለድ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ኢይገብራ ፡ ለኃጢአት ፡

ከእግዚአብሔር ፡ የተወለደ ። አንድም ፡ የተማረ ፡ ግን ፡ ኃጢአትን፡ አይሠራትም ፡

እስመ ፡ ዘርዐ ፡ ዚአሁ ፡

የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነውና ፡

ወቦቱ ፡ ይነብር ፡

በሱ ፡ አምኖ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራልና ። አን ድም ፡ ዘርዐ ፡ ዚአሁ ፡ ምእመን ፡ ቦቱ ፡ ይነብር ፡ በሱ ፡ አምኖ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራ ልና ። አንድም ፡ ዘርዐ ፡ ዚአሁ፡ ወንጌል ፡ በምእመን ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራልና ፡ (ጥቅ) ፡ ዘርዕሰ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ እንዲል ፡

ወኢይክል ፡ አብሶ ፡

መበደል፡አይቻለውም፡ አለ፡አይበድልም ፡

እስመ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ተወልደ ።

ከእግዚአብሔር ፡ ተወልዷል ፡ ከእግዚአ ብሔር ፡ ተምሯልና ፡ ቍ ፡ ፱ ፡ ም፡ ፭፡፲፰ ፡

፲ ፤ ወበዝንቱ ፡ እሙራን ፡ ውእቶሙ ፡ ደቂቀ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ወደቂቀ ፡ ጋኔን ፡

በዚህም ፡ ደቂቀ፡ እግዚአብሔርና፡ደቂቀ ፡ ጋኔን ፡ የተለዩ ፡ ናቸው፡ አለ፡ ይታወቃሉ፡

ኵሉ፡ዘኢይገብራ፡ለጽድቅ፡ኢኮነ፡እምእግዚአብሔር ፡

ጽድቅን ፡ የማይሠራ ፡ ሰው ፡ ከእግዚአ ብሔር ፡ የተወለደ ፡ የተማረ ፡ አይደለም ፡

ወከማሁ ፡ ዘኢያፈቅር ፡ ቢጾ ፡

ወንድሙንም ፡ የማይወድ ፡ ሰው ፡ ከእግ ዚአብሔር ፡ የተወለደ ፡ የተማረ ፡ አይ ደለም ።

፲፩ ፤ እስመ ፡ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ትእዛዝ ፡ እንተ ፡ ሰማ ዕክሙ ፡ ትካት ፡

በጥንተ ፡ ስብከት ፡ የሰማችኋት ፡ ትእዛዝ፡ ይህች ፡ ናትና ፡

ከመ ፡ ንትፋቀር ፡ በበይናቲነ ፡

እርስ ፡ በርሳችን ፡ ፍቅርን ፡ እንይዝ ፡ ዘንድ ፡ ነውና ፡ ዮሐ ፡ ፲፫ ፡ ፴፬ ።



www.ethiopianorthodox.org

፲፪ ፤ ወአኮ ፡ በከመ ፡ ቃየን ፡ ዘእምእኩይ ፡ ውእቱ ፡

ፍቅር ፡ መያዛችንም ፡ ከሰይጣን ፡ እንደ ፡ ተወለደ ፡ እንደ ፡ ተማረ ፡ እንደ ፡ ቃኤል ፡ አይደለም ፡

ወቀተሎ ፡ ለእኁሁ ፡

ወንድሙንም ፡ እንደ ፡ ገደለው ፡ እንደ ፡ ቃኤል ፡ አይደለም ፡ ነባሩን ፡ በዘማች ፡ አኀላው ፡ (ጥቅ)፡ ዘበኵሩ ፡ ወዘጸውዑ ፡ እ ንዲል ፡

ወበእንተ ፡ ምንት ፡ ቀተሎ ፡

ስለምን ፡ ገደለው ፡

እስመ ፡ ምግባረ ፡ ዚአሁ ፡ እኩይ ፡ ውእቱ ፡

እሱ ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ ነበረና ፡

ወዘእኁሁሰ ፡ ጻድቅ ፡ ውእቱ ።

ወንድሙ፡ ግን፡ ደግ፡ ሰው ፡ ነበረና፡ ስለም ን ፡ ገደለው ፡ ብሎ ፡ ያደንቃል ። አንድም፡ ስለምን ፡ ገደለው ፡ ብትል ፡ እሱ ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ ነበረና ፡ ወንድሙ ፡ ግን ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነበረና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። አንድም ፡ እሱ ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ ነበረና ፡ ወንድሙ ፡ ግን ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነበረና ፡ ስለምን ፡ ገደ ለው ፡ ብላችሁ ፡ አታድንቁ ፡ ዘፍጥ ፡ ፬ ፡ ፰ ። ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፴፭ ። ይሁዳ ፡ ቍ ፡ ፲፩ ።

፲፫ ፤ ወኢታንክሩ ፡ አኃዊነ ፡ እመኒ ፡ ዓለም ፡ ጸልአክሙ ።

ወንድሞቻችን ፡ ዓለሙ ፡ ቢጠላችሁ ፡ ዓ ለሙ ፡ እንደ ፡ ቃኤል ፡ እናንተ ፡ እንደ ፡ አቤል ፡ መሆናችሁ ፡ ነውና ፡ አታድንቁ ፡ ማቴ ፡ ፭ ፡ ፲፩ ። ዮሐ ፡ ፲፭ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ።

፲፬ ፤ ንሕነሰ ፡ ነአምር ፡ ከመ ፡ ዐደውነ ፡ እሞት ፡ ውስተ ፡ ሕይወት ፡

እኛስ ፡ ከሞት ፡ ወደ ፡ ሕይወት። አንድም፡ ከገሃነም ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እንድንሄድ ፡ እናውቃለን ፡

እስመ ፡ ናፈቅር ፡ ቢጸነ ፡

ወንድማችንን ፡ እንወዳለንና ፡

ወዘሰ ፡ ኢያፈቅር ፡ ቢጾ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ይነ ብር ።

ወንድሙን ፡ የማይወድ ፡ ግን ፡ በጨለማ ፡ በድንቁርና ፡ በገሃነም ፡ ይኖራል ፡ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፴፬ ። ም ፡ ፪ ፡ ፲፩ ። ዘሌዋ ፡ ፲፱ ፡ ፲፯ ።

፲፭ ፤ ኵሉ፡ ዘይጸልእ፡ ቢጾ፡ ቀታሌ፡ ነፍስ ፡ ውእቱ ፡

ወንድሙን፡ የሚጠላ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ነፍስ፡ ገዳይ ፡ ነው ። ሐተታ ፡ ወንድሙን ፡ ከጠ ላው ፡ ያማዋል ፡ ካማውም ፡ ከቀቲል ፡ ያደ ርሰዋልና ። አንድም ፡ ወንድሙን ፡ ከጠ ላው ፡ ምጽዋቱን ፡ ይነሣዋል ፤ ምጽዋቱ ንም ፡ ከነሣው ፡ ይሞታልና ፡ (ጥቅ) ፡ ሕይ ወቱ ፡ ለነዳይ ፡ ስኢለ ፡ ምጽዋት ፡ ዘሰ ፡ አበዮ ፡ ቀተሎ ፡ እንዲል ፡

ወተአምሩ ፡ ከመ ፡ ለቀታሌ ፡ ነፍስ ፡ አልቦ ፡ ሕይ ወት ፡ ዘለዓለም ፡ እንተ ፡ ትሄሉ ፡ ላዕሌሁ ።

ለነፍስ ፡ ገዳይ ፡ ተዋሕዳው፡ ያለች ፡ ነፍሱ በእሱ፡ ጸንታ፡ እንዳትኖር ፡ታውቃላችሁ ። ሐተታ ፡ ሊገሉት ፡ ይሹታልና ፡ ቢያገ ኙት ፡ ይገሉታልና። አንድም ፡ ኩን ፡ ድን ጉጸ፡ ወርዐደ፡ ባለው፡ ያፍ፡ በበረረ፡ ዘንግ፡ በተወረወረ ፡ ብር ፡ ብር፡ ሲል፡ ይኖራልና። አንድም ፡ በነፍስ ፡ የዘለዓለም ፡ ድኅነት ፡ እንደ ፡ ሌለው ፡ ታውቃላችሁ ፡ ማቴ ፡ ፭ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ።

፲፮ ፤ ወበዝንቱ ፡ አእመርናሁ ፡ ለተፋቅሮ ፡

በዚህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍቅሩ ፡ ደግ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አውቀን ፡

እስመ ፡ ውእቱ ፡ መጠወ ፡ ነፍሶ ፡ በእንቲአነ ፡

እሱ ፡ ስለኛ ፡ ቤዛ ፡ ሆኖ ፡ ሰውነቱን ፡ ለሕ ማም ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቷልና ፡



ወንሕነኒ ፡ ይደልወነ ፡ ንመጡ ፡ ነፍሰነ ፡ በእንተ ፡ ቢጽነ ።

እኛም ፡ ሰውነታችንን ፡ ስለ ፡ ወንድሞቻ ችን ፡ ቤዛ ፡ ለመከራው ፡ አሳልፈን ፡ ልን ሰጥ ፡ ይገባናል ፡ አለ ፡ ተላልፈን ፡ ልን ሞት ፡ ይገባናል ።

፲፯ ፤ ወዘቦቱ ፡ መንበርተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡

የዚህ ፡ ዓለም ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡

ወይሬኢ ፡ ቢጾ ፡ ጽኑሰ ፡ ወየዐጹ ፡ ምሕረቶ ፡ እም ኔሁ ።

ወንድሙን፡ ተቸግሮ ፡ አይቶ፡ ምጽዋቱን ፡ የከለከለው ፡

እፎ ፡ ይነብር ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕሌሁ ።

የእግዚአብሔር ፡ ፍቅሩ ፡ እንደምን ፡ ያድ ርበታል ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፳ ።

፲፰ ፤ ደቂቅየ ፡ ኢንትፋቀር ፡ በቃል ፡

ልጆቼ ፡ የቃል ፡ ዘመድ ፡ ከገቢያም ፡ አይ ገድ ፡ እንዲሉ ፡ በቃል ፡ ብቻ ፡

ወበልሳን ፡

በሐሰት ፡ ፍቅርን ፡ አንያዝ ፡

ዘእንበለ ፡ በምግባር ፡ ወበጽድቅ ፡

በሥራ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ አለ ፡ የጎደለውን ፡ በመምላት ፡ የጠመመውን ፡ በማቅናት ፡ ነው ፡ እንጅ ። ቃል ፡ ላለው ፡ ወበጽድ ቅ ፡ በእውነት ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ልሳን ፡ ላ ለው ፡ ያዕ ፡ ፩ ፡ ፳፪ና ፡ ፪ ፡ ፲፭ ።

፲፱ ፤ ወበዝንቱ፡ ነአምር፡ ከመ፡ እምጽድቅ፡ ንሕነ ፡

በዚህም ፡ ከጽድቅ ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ሆነ ። አንድም ፡ ከጌታ ፡ እንደ ፡ ተወለድነ ፡ እንደ ፡ ተማርነ ፡ እናውቃለን ፡

ወንሕነሰ ፡ ቅድሜሁ ፡ ናመክሮ ፡ ለልብነ ፡

እኛስ ፡ ከመስጠት ፡ አስቀድሞ ፡ ልቡና ችንን ፡ እንመርምረው ፡ በስስት ፡ ባሕር ፡ ይሰጥምብን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አይሰጥምብን፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስኔ ፡ ነግ ፡ በኔ ፡ ይህን ፡ ብ ሰጥ ፡ ምን ፡ እውጥ ፡ ሰጥቶ ፡ ይለምን ፡ ይልብን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አይልብንም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡

ወእመሰ ፡ ያርስሐስሐነ ፡ ልብነ ፡ እምአበሳነ ።

ልቡናችን ፡ በስስት ፡ ባሕር ፡ ቢሰጥም ብን ፡ ግን ፡ ስኔ ፡ ነግ ፡ በኔ ፡ ሰጥቶ ፡ ይለ ምን ፡ ይህን ፡ ብሰጥ ፡ ምን ፡ እውጥ ፡ ቢል ብን ።

፳ ፤ ወያዐብዮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለልብነ ፡

እምአበሳነ ፡ የዐብዮ ፡ ከኃጢአታችን ፡ የተነሣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልቡናችንን ፡ እምቢ ፡ ይለዋል ፡ አለ ፡ ያቀረበውን ፡ መ ሥዋዕት ፡ የጸለየውን ፡ ጸሎት ፡ አይቀ በለውም ፡

ወየአምር ፡ ኵሎ ።

እግዚአብሔር ፡ ሁሉን ፡ ያውቃልና ።

፳፩ ፤ አኃዊነ ፡ እመሰ ፡ ኢቀለየነ ፡ ልብነ ፡ ገጸ ፡ ብነ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

ወንድሞቻችን ፡ ልቡናችን ፡ በስስት ፡ ባ ሕር ፡ ባይሰጥምብን ፡ ስኔ ፡ ነግ፡ በኔ ፡ ይህ ን ፡ ብሰጥ ፡ ምን ፡ እውጥ ፡ ሰጥቶ ፡ ይለ ምን ፡ ባይልብን ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ባለሟልነት ፡ አለን ። አንድም ፡ (ወንሕነሰ) ፡ ፍዳ ፡ ከመቀበል ፡ አስቀ ድሞ ፡ ጥንቱን ፡ ኃጢአቱን ፡ ያውቅብን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ልቡናችንን ፡ እንመርምረው፡ (ወእመሰ) ፡ ከኃጢአታችን ፡ የተነሣ ፤ ልቡናችን፡ ርሱሐን ፡ ናችሁ፡ ቢለን ፡ ግን ፡ (ያዐብዮ) ፡ እግዚአብሔር ፡ ልቡናችንን ፡ ያከብረዋል ፡ አለ ፡ ያቀረበውን ፡ መሥዋ ዕት ፡ የጸለየውን ፡ ጸሎት ፡ ይቀበለዋል ፤ (ወየአምር) ፡ ሁሉንም ፡ እንዲያውቅ ፡ ያደርገዋል ። (ወእመሰ ፡ ኢቀለየነ) ፡ ልቡ

www.ethiopianorthodox.org

ናችን ፡ ቢዘልፈን ፡ ግን ፡ አለ ፡ ቢያውቅ ብን፡ ኃጢአቱን፡ ነው ፤ (ጥቅ) ፡ ይቀልየከ፡ ልብከ ፡ ሳሚ ፡ ወልደ ፡ ጌራ ፡ እንዲል ። (ብነ ፡ ገጽ) ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ባ ለሚልነት ፡ አለን ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፳፫ና ፡ ፬ ፡ ፲፯ ። ሮሜ ፡ ፷ ፡ ፩፡ ፪ ። ዕብ ፡ ፬ ፡ ፲፯ ።

፳፪ ፤ ወዘሂ ፡ ሰአልናሁ ፡ ንነሥእ ፡ እምኀቤሁ ፡

የለመነውንም ፡ ከሱ ፡ ዘንድ ፡ እንቀበላ ለን ፡ አለ ፡ ይሰጠናል ፡

እስመ ፡ ትእዛዘ ፡ ነዐቅብ ፡

ሕጉን ፡ እንጠብቃለንና ፡

ወንገብር ፡ ዘይኤድሞ ፡ ቅድሜሁ ፡

ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ እንሠራለንና ፡ ማር ፡ ፲፩ ፡ ፳፬ ።

፳፫ ፤ ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ትእዛዙ ፡

ትእዛዙም ፡ ይህች ፡ ናት ፡

ከመ ፡ ንእመን ፡ በወልዱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡

በባሕርይ፡ ልጁ፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ እና ምን፡ ዘንድ፡ ነው ፡ እንጅ ። እንድናምን ፡ ትእዛዙ ፡ ነው፡ እንድናምን፡ መሆን፡ ነው፡

ወንትፋቀር ፡ በበይናቲነ ፡

እርስ ፡ በርሳችን ፡ ፍቅርን ፡ እንይዝ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

በከመ ፡ ወሀበነ ፡ ትእዛዘ ፡

ደቂቅየ፡ ተፋቀሩ፡ ብሎ፡ ትእዛዙን፡ እንደ ፡ ነገረን ፡ ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፳፱ ። ማር፡ ፲፪ ፡ ፴፩ ።

፳፬ ፤ ወዘሰ ፡ የዐቅብ ፡ ትእዛዞ ፡ ቦቱ ፡ ይነብር ፡

ሕጉን ፡ የሚጠብቅ ፡ ግን ፡ ተዋሕዶት ፡ ይኖራል ።

ወውእቱኒ ፡ ቦቱ ፡

ጌታም ፡ አድሮበት ፡ ይኖራል ፤ ሕጹፅ ፡ የጸጋ ፡ ተዋሕዶ ፡ እንደ ፡ ብረትና ፡ እንደ፡ እሳት ።

ወበዝንቱ ፡ ነአምር ፡ ከመ ፡ ይነብር ፡ ምስሌነ ፡ እምነ፡ መንፈሱ ፡ ቅዱስ ፡ ዘወሀበነ ።

ከሰጠን ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዕውቀትን ፡ ነሥተን ፡ አድሮብን ፡ እንዲኖር ፡ በዚህ ፡ እናውቃለን ። (ጥቅ) ፡ ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ ብሂለ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ፡ ዘእንበለ ፡ ዘመ ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕሌሁ ፡ እንዲል ። አ ንድም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ልጅች ፡ አድርጎ ፡ (ይነብር) ፡ አድሮብን ፡ እንዲ ኖር ፡ እናውቃለን ። (ጥቅ) ፡ ወየኀድር ፡ ላዕሌነ ፡ ዘቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ተፍጻሜት ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንዲል ። አንድም ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ አድሮብን ፡ እንዲኖር ፡ እናውቃለን ። (ጥቅ)፡ እመ፡ ቦ፡ ዘዐቀበ ፡ ቃልየ ፡ አነ ፡ ወአቡየ ፡ ወመን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ንመጽእ ፡ ኀቤሁ ፡ ወንገብ ር ፡ ምዕራፈ ፡ ውስቴቱ ፡ እስመ ፡ ስብሐ ቲሁ ፡ ወኀይሉ ፡ የዐርፍ ፡ ላእሌክሙ ፡ ዘ ያፈቅረኒ ፡ ይዕቀብ ፡ ቃልየ ፡ ወያፈቅሮ ፡ አቡየ ፡ እንዲል ፡ ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፳፫ ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩ ፤ አኀዊነ ፡ ለኵሉ ፡ መንፈስ ፡ ኢትእመኑ ፡

ወንድሞቻችን ፡ ሐሰተኛ ፡ መምህርን ። አንድም ፡ ሐሰተኛ ፡ ትምህርትን ፡ አትመ ኗት ፡

አላ ፡ አመክርዋ ፡ ለመንፈስ ፡ ለእመ ፡ እምኀበ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ይእቲ ፡

መምህራቱ፡ ከእግዚአብሔር፡ የተማረች ፡ ትምህርቲቱ፡ ከእግዚአብሔር፡ የተገኘች ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ መርምሯት ፡ እንጅ ። አን ድም ፡ መምህርን ፡ ትምህርትን ፡ አት መኑ ፡ ትምህርቱ ፡ መምህሩ ፡ ከእግዚአብ ሔር ፡ የተማረ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መርምሩ ፡ እንጅ ፡

እስመ ፡ ብዙኃን ፡ ሐሳውያነ ፡ ነቢያት ፡ መጽኡ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ እለ ፡ ኢየአምኑ ፡ በኢየሱስ ፡ ክር ስቶስ ።

ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ የማያውቁ ፡ ነቢ ያትን ፡ የሚያሳብሉ ፡ በነቢያት ፡ የሚያ ብሉ ፡ ብዙ ፡ ሐሰተኞች ፡ መምህራን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ተነሥተዋልና ።

፪ ፤ ወበዝንቱ ፡ ተአምርዋ ፡ ለመንፈሰ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ወለመንፈሰ ፡ ሐሰት ፡

በዚህም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተማረች ውን ፡ መምህርና ፡ ከሰይጣን ፡ የተማረ ችውን ፡ መምህር ። አንድም ፡ ከእግዚአ ብሔር ፡ የተገኘችውን ፡ ትምህርትና ፡ ከሰይጣን ፡ የተገኘችውን ፡ ትምህርት ። አንድም ፡ እውነተኛይቱን ፡ ትምህርትና ፡ ሐሰተኛይቱን ፡ ትምህርት ፡ እውነተኛይ ቱን ፡ መምህርና ፡ ሐሰተኛይቱን ፡ መምህ ር ፡ ታውቋታላችሁ ፡

ኵላ ፡ መንፈስ ፡ እንተ ፡ ተአምን ፡ ከመ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መጽአ ፡ በሥጋ ፡ ሰብአ ፡ እምነ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ይእቲ ፡

ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ የምታምን ፡ መምህር ፡ የም ታሳምን ፡ ትምህርት ፡ መምህሪቱ ፡ ከእ ግዚአብሔር ፡ የተማረች ፡ ትምህርቲቱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘች ፡ ናት ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፫ ።

፫ ፤ ወኵላ ፡ መንፈስ ፡ እንተ ፡ ኢተአምን ፡ በኢየ ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ መጽአ ፡ በሥጋ ፡ ሰብእ ፡ ኢ ኮንት ፡ እምነ ፡ እግዚአብሔር ፡

ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ በሥጋ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማያምን ፡ መምህር ፡ የማያሳምን፡ ትምህርት ፡ ግን ፡ መምህሩ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተማረ ፡ ትምህርቱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘ ፡ አይደለም ፡

ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ሐሳዌ ፡ መሲሕ ፡ ዘሰማዕክሙ ፡ ከመ ፡ ይመጽእ ፡

እንዲነሣ ፡ የሰማችሁት ፡ መሲሕ ፡ ክር ስቶስን ፡ የሚያሳብል ። አንድም ፡ በመ ሢሕ ፡ በክርስቶስ፡ የሚያብል ። አንድም፡ ሐሳዊ ፡ መሲሕ ፡ ይላል ፡ ሐሰተኛ ፡ መ ምህር ፡ ይህ ፡ ነው ።

ወይእዜኒ ፡ ወድአ ፡ መጽአ ፡

ኋላ ፡ ከሁሉ ፡ ደርሶ ፡ እንዲገለጽ ፡ ተገ ልጾ ፡ ከሁሉ፡ እንዲደርስ ፡ ዛሬም፡ ፈጽሞ ፡ ተገልጾአል ፡

ወውስተ ፡ ዓለም ፡ ሀሎ ።

ከሁሉ ፡ ደርሷል ።

፬ ፤ ወአንትሙሰ ፡ እምነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አን ትሙ ፡ ደቂቅየ ፡

ልጆቼ ፡ እናንተስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተ ወለዳችሁ ፡ የተማራችሁ ፡ ናችሁ ፡

ወሞእክምዎ ፡ ለእኩይ ፡

እኩይ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋን ። አንድም፡ እኩይ ፈቃደ ፡ ሰይጣንን፡ ድል ፡ ነሥታችኋልና ፡

እስመ ፡ የዐቢ ፡ ዘሀሎ ፡ ምስሌክሙ ፡ እምነ ፡ ዘው ስተ ፡ ዓለም ፡ ሀሎ ።

በዓለሙ ፡ አድሮ ፡ ካለ ፡ ሀብተ ፡ ሰይጣን ፡ በናንት ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይበልጣልና ። አንድም፡ በዓለሙ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ ሀብተ ፡ ሰይጣን ፡ በናንተ ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ፡ ፪ ፡ ነገሥ ፡ ፯ ፡ ፲፯ ። ፩ ፡ ዜና ፡ ፴፪ ፡ ፯ ።



www.ethiopianorthodox.org

፭ ፤ ወእሙንቱሰ ፡ እምነ ፡ ዓለም ፡ እሙንቱ ፡

እሊያስ ፡ ከዓለም ፡ የተገኙ ፡ ዓለማውያን፡ ናቸው ፡

ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ እምነ ፡ ዓለም ፡ ይነብቡ ፡

ስለዚህ ፡ ዓለማዊ ፡ ትምህርትን ፡ ያስተም ራሉ ።

ወዓለሙኒ ፡ ይሰምዖሙ ።

ዓለሙም ፡ ይቀበላቸዋል ፡ (ጥቅ) ፡ እስመ፡ ዓለም ፡ ያፈቅር ፡ እሊዓሁ ፡ እንዲል ፡ ሌባ ፡ ሌባውን ፡ ወንበዴ ፡ ወንበዴውን ፡ ይወዳልና ፡ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፴፩ና ፡ ፲፫ ፡ ፲፱ ።

፮ ፤ ወንሕነሰ ፡ እምነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንሕነ ፡

እኛ ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተወለድነ፡ ከእግዚአብሔር፡ የተማርነ ፡ ነንና ፡ ዓለ ማዊ ፡ ትምህርትን ፡ አናስተምርም ፡

ወዘየአምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሰምዐነ ፡

እግዚአብሔርን ፡ የሚያምነው ፡ የሚወ ደው ፡ ትምህርታችንን ፡ ይቀበለናል ፡

ወዘኢኮነ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ኢይሰምዐነ ፡

ከእግዚአብሔር ፡ ያልተማረ ፡ ያልተወ ለደ፡ግን ፡ ትምህርታችንን፡ አይቀበለንም ፡

ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ነአምራ ፡ ለመንፈሰ ፡ ጽድቅ ፡ ወለመንፈሰ ፡ ሐሰት ።

በዚህም፡እውነተኛይቱን፡ ትምህርትና፡ ሐ ሰተኛይቱን፡ ትምህርት፡እውነተኛይቱን ፡ መምህርና ፡ ሐሰተኛይቱን ፡ መምህር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘችውን ፡ ትምህ ርትና ፡ ከሰይጣን ፡ የተገኘችውን ፡ ትም ህርት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተማረችውን ፡ መምህርና ፡ ከሰይጣን ፡ የተማረችውን ፡ መምህር ፡ እናውቃለን ፡ ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፴፯ ።

፯ ፤ አኃዊነ ፡ ለንትፋቀር ፡ በበይናቲነ ፡

ወንድሞቻችን ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ ፍቅ ርን ፡ እንያዝ ፡

እስመ ፡ ተፋቅሮ ፡ እምነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ።

ፍቅር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘ ፡ ነውና ፡

ወኵሉ ፡ ዘይትፋቀር ፡ እምነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ተወልደ ፡

ፍቅርን ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከእግዚአብ ሔር ፡ የተወለደ ። አንድም ፡ የተማረ ፡ ነው ፡

ወየአምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርን ፡ ያውቀዋል ፡ ይወደዋል።

፰ ፤ ወዘሰ ፡ ኢያፈቅር ፡ ቢጾ ፡ ኢየአምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

ፍቅርን ፡ የማይዝ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔ ርን ፡ አያውቀውም ፡ አይወደውም ፡

እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ውእቱ ፡

እግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ነውና ። ሐተታ ፡ በባሕርዩ ። አንድም፡ አድሮ፡ የሚያፋቅር፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በግብሩ ፡ ፍቅር ፡ ብሎታል ።

፱ ፤ ወበዝንቱ ፡ ተዐውቀ ፡ ፍቅሩ ፡ ለእግዚአብሔር፡ ላዕሌነ ፡

በዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለኑ ፡ ለኛ ፡ ታወቀ ። አንድም ፡ (ኪ ያነ) ፡ እግዚአብሔር ፡ እኛን ፡ መውደዱ ፡ በዚህ ፡ ታወቀ ፡

እስመ ፡ ለወልዱ ፡ ዋሕድ ፡ ፈነዎ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡

ተቀዳሚ ፡ ተከታይ ፡ የሌለው ፡ የባሕ ርይ፡ ልጁን፡ ወደዚህ፡ ዓለም፡ ሰዶታልና ፡

ከመ ፡ ንሕዮ ፡ በእንቲአሁ ።

እሱ ፡ ስለ ፡ ካሰልን ፡ እንድን ፡ ዘንድ ፡ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ። ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ።

፲ ፤ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ፍቅሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

የእግዚአብሔር ፡ ፍቅሩ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለ፤ ፍቅር ፡ መሆኑ ። አንድም ፡ እኛን ፡ መው ደዱ ፡ ይህ፡ ነው፡



አኮ ፡ ንሕነ ፡ ዘአፍቀርናሁ ፡ አላ ፡ ውእቱ ፡ አፍቀረነ ፡

አስቀድሞ ፡ እኛ ፡ የወደድነው ፡ አይደ ለም ፡ እሱ ፡ ወደደን ፡ እንጂ ፡

ወፈነዎ ፡ ለወልዱ ፡ ይኅድግ ፡ ለነ ፡ ኃጣውኢነ ።

ፍቅሩም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ኃጢአታችንን ፡ ይቅር ፡ ይለን ፡ ዘንድ ፡ የባሕርይ ፡ ልጁን ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ሰዶታልና ፡ ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፲ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲፱ ፡ ቆላ ፡ ፩ ፡ ፳ ።

፲፩ ፤ አኃዊነ ፡ እመሰ ፡ ከመዝ ፡ አፍቀረነ ፡ እግዚአብሔር ፡

ወንድሞቻችን ፡ እግዚአብሔርስ ፡ ልጁን፡ እስከ ፡ መስጠት ፡ ድረስ፡ ደርሶ ፡ እንዲህ ፡ ከወደደን፡

ወንሕነኒ ፡ ይደልወነ ፡ ንትፋቀር ፡ በበይናቲነ ፡

እኛም ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ ፍቅርን ፡ ልን ይዝ ፡ ይገባናል ፡ ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፴፫ ።

፲፪ ፤ ለእግዚአብሔርሰ ፡ አልቦ ፡ ዘርእዮ ፡ ግሙራ ፡

ያውስ ፡ ቢሆን ፡ የወደደን ፡ እግዚአብሔ ርን ፡ እንወዳለን ፡ እንጂ ፡ ያልወደደን ፡ ሰውን ፡ እንወዳለን፡ ትሉኝ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እግዚአብሔርንስ ፡ ከቶ ፡ ያየው ፡ የለም ። ሐተታ ፡ እስመ ፡ በአንጽሖ ፡ መንፈስ ፡ ርእይዎ ፡ ነቢያት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይል ፡ የለም ፡ ቢሉ ፡ በዘፈቀደ ፡ ባሕርዩ ፡ ተገልጾላቸው ፡ ያዩትን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ እሳት ፡ ዛፍ ፡ ገደል ፡ አየሁ ፡ እንደ ፡ ማለ ት ፡ ነው ፡ እንጂ፡ በባሕርዩ ፡ ያየው ፡ የለምና ። አንድም ፡ እግዚአብሔርንስ ፡ ከቶ ፡ ቀዶ ፡ ያለበሰው ፡ ቆርሶ ፡ ያጐረ ሰው ፡ የለም ፡

ወእመሰ ፡ ተፋቀርነ ፡ በበይናቲነ ፡

እርስ ፡ በርሳችን ፡ ፍቅርን ፡ ብንይዝ ፡ (ከየ ዝነ ፡ ግን) ፡

እግዚአብሔር ፡ ይነብር ፡ ምስሌነ ፡

ብነ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ አድሮ ብን ፡ ይኖራል ፡

ወፍቅሩሂ ፡ ፍጹም ፡ ሀሎ ፡ ምስሌነ ።

ፍጹም ፡ ፍቅሩም ፡ በኛ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል። ዘፀአ ፡ ፴፫ ፡ ፳። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፰ ። ፩ ፡ ጢሞ፡ ፮ ፡ ፲፮ ።

፲፫ ፤ ወበዝንቱ ፡ ነአምር ፡ ከመ ፡ ምስሌሁ ፡ ንነ ብር ፡

በዚህም ፡ ተዋሕደን ፡ እንድንኖር ፡ እና ውቃለን ፡

ወውእቱኒ ፡ ምስሌነ ፡

እሱም ፡ አድሮብን ፡ እንዲኖር ፡ እናውቃ ለን ። ሐተታ ፡ እንደ ፡ እሳትና ፡ እንደ ፡ ብረት ፡ ሕጹፅ ፡ የጸጋ ፡ ተዋሕዶ ።

እምነ ፡ መንፈሱ ፡ ቅዱስ ፡ ዘወሀበነ ።

ከሰጠን ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዕውቀትን ፡ ነሥተን ፡ ነአምር ፡ አድሮብን ፡ እንዲኖር፡ እናውቃለን ፡ (ጥቅ) ፡ ወየኀድር ፡ ላዕሌነ ፡ ዘቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ተፍጻሜት ፡ በመን ፈስ፡ ቅዱስ፡ እንዲል፡ አንድም ፡ በሰጠን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ልጅነት፡ አድርጎ ፡ አድ ሮብን ፡ እንዲኖር ፡ (አጥ) ፡ ወአልቦ ፡ ዘይ ክል፡ ብሂለ ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ዘእንበለ ፡ ዘመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕሌሁ ፡ እንዲል ። አንድም፡ ከሰጠን ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ አድሮብን ፡ እንዲኖር፡ እናውቃለን፡ እመ፡ ቦ ፡ ዘዐቀበ፡ ቃልየ፡ አነ ፡ ወአቡየ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ንመጽእ ፡ ኀቤሁ ፡ ወ ንገብር ፡ ምዕራፈ ፡ ውስቴቱ ፡ እንዲል ።

፲፬ ፤ ወንሕነኒ ፡ ርኢነ ፡ ወሰማዕነ ፡ ከመ ፡ አብ ፡ ፈነወ ፡ ወልዶ ፡ መድኅነ ፡ ዓለም ፡

እኛም ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ የባሕርይ ፡ ልጁን ፡ የዘለዓለም ፡ ድኅነት ፡ አድርጎ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እንደ ፡ ሰደደው ፡ አውቀን ፡ አምነናል ፡ መስክረናል ።

፲፭ ፤ ወኵሉ ፡ ዘየአምን ፡ ከመ ፡ ኢየሱስ ፡ ውእቱ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡

ኢየሱስ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚያምን ፡ ሁሉ ፡

እግዚአብሔር ፡ ይነብር ፡ ምስሌሁ ፡

ቦቱ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ አድሮበት ፡ ይኖራል ፡

ወውእቱኒ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ።

እሱም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ፡ ተዋሕዶ፡ ይኖራል ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፳ ።

፲፮ ፤ ወንሕነሰ ፡ አእመርነ፡ ወአመነ፡ እንተ፡ ቦ ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌነ ፡

ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደረብን ፡ እኛ ፡ አውቀን ፡ ተረድተን ፡ አምነናል ። አንድም ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ አድሮብን ፡ እንዳለ ፡ አውቀን ፡ ተረድተን ፡ አምነናል ። አንድም ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደረበት ፡ ሰው ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አውቀን ፡ ተረድተን ፡ አምነናል ። አንድም ፡ በኛ ፡ አድሮ ፡ ያለውን ፡ ፍቅረ፡ እግዚአብሔርን ፡አውቀን ፡ ተረድተን ፡ አምነናል ፡

እግዚአብሔርሰ ፡ ፍቅር ፡ ውእቱ ፡

እግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ነውና ፡

ወዘኒ ፡ ነበረ ፡ በተፋቅሮ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይነብር ፡

በፍቅር ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዶ ፡ ይኖራል ።

ወእግዚአብሔርኒ ፡ ምስሌሁ ።

እግዚአብሔርም ፡ አድሮበት ፡ ይኖራል ።

፲፯ ፤ ወበዝንቱ ፡ ትትፌጸም ፡ ፍቅሩ ፡ ምስሌነ ፡

በዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ እኛን ፡ መውደዱ ፡ ይፈጸምልናል ።

ከመ ፡ ንርከብ ፡ ገጸ ፡ በዕለተ ፡ ደይን ፡ በኀቤሁ ፡

በቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ ቀን ፡ ከእሱ፡ ዘንድ፡ ባለሟልነትን ፡ እናገኝ ፡ ዘንድ ፡

እስመ ፡ በከመ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ኮነ፡ ንሕነኒ ፡ ውስተ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ እሱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁነናልና ። ም ፡ ፫ ፡ ፳፩ ።

፲፰ ፤ ወአልቦ ፡ ፍርሀት ፡ ውስተ ፡ ተፋቅሮትነ ፡

እስመ ፡ በከመ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ንሕነኒ ። ኮነ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ብሎ ፡ ነበረና ። በፍቅራችን ፡ ሰኔ ፡ ነግ ፡ በኔ ፡ ይህን ፡ ብሰጥ ፡ ምን ፡ እውጥ ፡ ሰጥቶ ፡ ይለምን ፡ ማለት ፡ የለባትም ። አንድም ፡ አይኑርባት ፡

አላ ፡ ተፋቅሮሰ ፡ ፍጽምት ፡ አፍአ ፡ ታወጽአ ፡ ለፍርሀት ፡

ፍጹም ፡ ፍቅርስ ፡ ሰኔ ፡ ነግ ፡ በኔ ፡ ይህን ፡ ብሰጥ ፡ ምን ፡ እውጥ ፡ ሰጥቶ ፡ ይለምን ፡ ማለትን ፡ ትርቃታለች ። አንድም ፡ ታርቃታለች ፡ እንጅ ፡ የለባትም ። አንድም ፡ ታርቃት ፡ እንጅ ፡ አይኑርባት ፡

እስመ ፡ ፍርሀትሰ ፡ መቅሠፍት ፡ ባቲ ፡

ይህን ፡ ብሰጥ ፡ ምን ፡ እውጥ ፡ ሰኔ ፡ ነግ ፡ በኔ ፡ ሰጥቶ ፡ ይለምን ፡ ማለትስ ፡ ርኅብኩ፡ ወኢያብላዕክሙ ፡ አስኼታ ፡ ሖሩ ፡ እምኔየ ፡ መባልን ፡ የምታመጣ ፡ ናት ፡ (ታሰኛለችም ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡

ወዘሰ ፡ ይፈርህ ፡ ኢኮነ ፡ ፍጹመ ፡ በተፋቅሮ ፡

ሰኔ ፡ ነግ ፡ በኔ ፡ ይህን ፡ ብሰጥ ፡ ምን ፡ እውጥ ፡ ሰጥቶ ፡ ይለምን ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ግን ፡ በፍቅር ፡ ፍጹም ፡ አይደለም ።

፲፱ ፤ ወንሕነኒ ፡ ንትፋቀር ፡ በበይናቲነ ፡

እኛ ፡ ግን ፡ ሰኔ ፡ ነግ ፡ በኔ ፡ ይህን ፡ ብሰጥ ፡ ምን ፡ እውጥ ፡ ሰጥቶ ፡ ይለምን ፡ ማለት ፡



ሳይኖርብን ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ ፍቅርን ፡ እንያዝ ። አንድም ፡ (ወአልቦ) ፡ በፍቅራችን ፡ እሱን ፡ ያገኘ ፡ ያገኘናል ፡ ማለት ፡ የለባትም ። አንድም ፡ አይኑርባት ፡ ፍጹም ፡ ፍቅርስ ፡ እሱን ፡ ያገኘ ፡ ያገኘናል ፡ ማለትን ፡ ታርቃታለች ። አንድም ፡ ታርቃታለች ፡ እንጅ ፡ አይኑርባት ፡ እሱን ፡ ያገኘ ፡ ያገኘናል፡ ማለትስ፡ ነግደ ፡ ኮንኩ፡ ወኢተወከፍክሙኒ ፡ አስኼታ፡ ሖሩ ፡ እምኔየ ፡ ታሰኛለች ፡ እኛ ፡ ግን ፡ እሱን ፡ ያገኘ ፡ ያገኘናል ፡ ሳንል ፡ ፍቅርን ፡ እንያዝ። ታሪክ ፡ በቀላውድዮስ ፡ ቄሣር ፡ ዘመን ፡ ጽኑ ፡ ረኃብ ፡ ሆነ ፡ በኔ ፡ ዘመን ፡ ረኃብ ፡ የሆነ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቅ ፡ እኩያን ፡ ሰቃልያነ ፡ አምላክ፡ አይሁድ ፡ በከተማህ ፡ አሉና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ አሉት ። ይሰደዱ ፡ ብሎ ፡ ዐዋጅ ፡ ነገረ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እነሱን ፡ ያገኘ ፡ ያገኘናል ፡ የሚል ፡ የማይቀበላቸው፡ ሆኗል፡ የማይል ፡ ግን ፡ ሚቀበላቸው ፡ ሆኗል ፡

ወናፍቅሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርን ፡ እንውደደው ፡

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ቀደመ ፡ አፍቅሮተነ ።

እሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ወዶናልና ።

፳ ፤ ወእመሰ፡ ቦ ፡ ዘይብል፡ አፈቅሮ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወይጸልእ ፡ ቢጾ ፡

እግዚአብሔርን ፡ እወደዋለሁ ፡ የሚል ፡ ወንድሙን ፡ የሚጠላ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡

ሐሳዊ ፡ ውእቱ ፡

ሐሰተኛ ፡ ነው ፡

እስመ ፡ ዘያፈቅሮ ፡ ለቢጹ ፡ ዘይሬኢ ፡ ለእግዚአብሔርኒ ፡ ያፈቅሮ ፡ ዘኢይሬኢ ።

የሚያየውን ፡ ወንድሙን ፡ የሚወድ ፡ የማያየውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይወደዋልና ፡ ንትፋቀር ፡ ሳለው ፡

ወዘሰ ፡ ኢያፈቅር ፡ ቢጾ ፡ ዘይሬኢ ፡ እፎ ፡ እንከ ፡ ይክል ፡ አፍቅሮቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘኢይሬኢ ።

የሚያየውን ፡ ወንድሙን ፡ የሚጠላ፡ ግን፡ የማያየውን ፡ እግዚአብሔርን፡ አይወደውምና ፡ ሐሳዊ ፡ ውእቱ ፡ ሳለው ። አንድም ፡ የሚያየውን ፡ ወንድሙን ፡ የሚወድ ፡ የማያየውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይወደዋል ። የሚያየውን ፡ ወንድሙን ፡ የሚጠላ ፡ ግን ፡ የማያየውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደምን ፡ እወደዋለሁ ፡ ይላል ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፬ ፡ ፲፩ ።

፳፩ ፤ ወዝንቱ ፡ ትእዛዝ ፡ እንተ ፡ ብነ ፡ እምኔሁ ፡

ከሱ ፡ የተቀበልነው ፡ ትእዛዝ ፡ አለን ።

ከመ ፡ ናፍቅሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርን ፡ እንወደው ፡ ዘንድ ፡

ወናፍቅር ፡ ቢጸነ ፡

ወንድማችንንም ፡ እንወድ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚወድ ፡ ወንድሙን ፡ ይወዳልና ፡ ማር ፡ ፲፪ ፡ ፴፩ ።

## ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፩ ፤ ኵሉ ፡ ዘየአምን ፡ ከመ ፡ ኢየሱስ ፡ ውእቱ ፡ መሢሕ ፡ እምነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተወልደ ፡

ኢየሱስ፡መሢሕ፡እንደ፡ ሆነ፡ አለ፡ ሥጋን፡ እንደ፡ተወሐደ፡የሚያምን፡ሁሉ፡ ከእግዚአብሔር፡ የተማረ። አንድም፡የተወለደ፡ነው፡

ወኵሉ ፡ ዘያፈቅሮ ፡ ለወላዲ ፡ ያፈቅር ፡ ዘኒ ፡ ተወልደ ፡ እምኔሁ ፡

ወላዲውን ፡ አብን ፡ የሚወደው ፡ ተወላዲውን ፡ ወልድን ፡ ይወዳል ። አንድም ፡ ወላዲውን ፡ ወልድን ፡ የሚወድ ፡ ተወላዲ

www.ethiopianorthodox.org

ውን ፡ ምእመንን ፡ ይወዳል ፡ ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፲፬ ፡ ፲፫ ።

፬ ፤ ወበዝንቱ ፡ ነአምር ፡ ከመ ፡ ናፈቅር ፡ ለወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሶበ ፡ አፍቀርናሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

ሶበ ፡ አፍቀርናሁ ፡ ለወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነአምር ፡ ከመ ፡ ናፈቅሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ (ብለህ ፡ ግጠም) ፡ ተወላዲውን ፡ ወልድን፡ በወደድነው፡ ጊዜ፡ ወላዲውን ፡ አብን ፡ እንድንወደው ፡ እናውቃለን ። አንድም ፡ ተወላዲውን ፡ ምእመንን ፡ በወደድነው ፡ ጊዜ ፡ ወላዲውን ፡ ወልድን፡ እንድንወደው ፡ እናውቃለን ፡

ወገበርነ ፡ ትእዛዞ ፡

ትእዛዙን ፡ እንደ ፡ ጠበቅን ፡ እናውቃለን ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፲፱ ።

፫ ፤ እስመ ፡ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ፍቅሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

የእግዚአብሔር ፡ ፍቅሩ ፡ ይህች ፡ ናትና ፡

ከመ ፡ ንዕቀብ ፡ ትእዛዞ ፡

ትእዛዙን ፡ እንጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ነውና ፡

ወትእዛዙኒ ፡ ኢኮነ ፡ ክቡደ ፡

ትእዛዙም ፡ ክቡድ ፡ አይደለም ፡ ስጡ ፡ ይስጧችሁ ፡ ውደዱ፡ ይውደዷችሁ፡ ነው፡ ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፲፫፡ ፳፫፡ ፳፬ ። ማቴ ፡ ፲፩፡ ፴ ።

፬ ፤ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘተወልደ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ይመውኦ ፡ ለዓለም ፡

ከእግዚአብሔር ፡ የተማረ። አንድም ፡ የተወለደ ፡ ዓለሙን ፡ ድል ፡ ይነሣዋልና ፡ አለ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋን ። አንድም ፡ ፈቃደ ፡ ሰይጣንን ፡ ድል ፡ ይነሣልና ፡

ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ሙዓቱ ፡

ድል ፡ መንሳቱም ፡ ይህች ፡ ናት ፡

እንተ ፡ ሞዖ ፡ ለዓለም ፡ ሃይማኖትክሙ ።

ዓለሙን ፡ ድል ፡ የነሣው፡ ሃይማኖታችሁ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ማመናችሁ፡ ናት ። አንድም ፡ ሃይማኖታችሁ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዓለሙን ፡ ድል ፡ የነሣው ፡ መንሣት ፡ ናት ። አንድም ፡ ሃይማኖታችሁ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ድል ፡ የነሣው ፡ ዓለሙን ፡ ድል ፡ መንሣት ፡ ናት ፡ ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፲፫ ። ዮሐ ፡ ፲፮ ፡ ፴፫ ፡

፭ ፤ ወመኑ ፡ ውእቱ ፡ ዘይመውዖ ፡ ለዓለም ፡

ዓለሙን ፡ ድል ፡ የሚነሣው ፡ ማነው ፡

ዘእንበለ ፡ ዘየአምን ፡ ከመ ፡ ኢየሱስ ፡ ውእቱ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡

ኢየሱስ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሚያምን ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ የሚያምን ፡ ሰው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በውኃ ፡ ሲያጥብ ፡ በደሙ ፡ ሲያነጻ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሲያከብር ፡ እንዲመጣ ፡ ይናገራል ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፬ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፶፯።

፮ ፤ ወከመ ፡ ውእቱ ፡ መጽአ ፡ በማይ ፡ ወበደም ፡ ወበመንፈስ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ በውኃ ፡ ሲያጥብ ፡ በደሙ፡ ሲያነጻ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሲያከብር ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ የሚያምን ፡ ነው ፡ እንጅ። አንድም ፡ ከሚያምን፡ ሰው፡ በቀር ፡

ወአኮ ፡ በማይ ፡ ባሕቲቱ ።

በውኃ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡

አላ ፡ በማይኒ ።

የዕለት ፡ ፅንስ ፡ በመሆን ፡ ነው ፡ እንጅ ፡

ወበደምኒ ፡

በደማዊ ፡ አካል ፡ በመገኘት፡ ነው፡ እንጅ፡

ወበመንፈስ ፡ ውእቱ ፡ ዘስምዐ ፡ ይከውን ፡ ከመ ፡ መንፈስ ፡ ጽድቅ ።

የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሚመሰክር ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡ እንጅ ። አንድም ፡ አኮ ፡ በማይ ፡ የዕለት ፡ ፅንስ ፡



በመሆን ፡ ብቻ ፡ አይደለም፡ (አላ ፡ በማይኒ)፡ በማየ ፡ ዮርዳኖስ ፡ በመጠመቁም ፡ ነው፡ እንጅ፡ (ወበደምኒ)፡ በደማዊ፡ አካል፡ በመገለጹ ፡ ነው ፡ እንጅ ። ወበመንፈስ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚመሰክር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በርግብ ፡ አምሳል ፡ ወርዶ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ በመቀመጡ ፡ ነው ፡ እንጅ ። አንድም፡ አኮ፡ በማይ፡ በማየ ፡ ዮርዳኖስ፡ በመጠመቁ፡ ብቻ፡ አይደለም ፤ በማየ ፡ ገቦ፡ ነው፡ እንጅ። በደመ፡ ገቦ፡ ነው፡ እንጅ፡በመንፈስ፡ ልደት፡ ነው ፡ እንጅ።አንድም፡ (አኮ፡በማይ)፡ በማየ፡ገቦ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ካህናት ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ በሚለውጡት፡ ማየ፡ ገቦም፡ ነው፡ እንጅ ። (ወበደምኒ)፡ በደመ፡ ገቦ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ካህናት ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ በሚለውጡት ፡ ደመ ፡ ገቦ ፡ ነው ፡ እንጅ ። ወበመንፈስ ፡ በመንፈስ ፡ ልደት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ካህናት ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ በሚያሰጡት ፡ መንፈስ ፡ ልደት ፡ ነው ፡ እንጅ ። አንድም ፡ (አኮ) ፡ በማየ ፡ ምንዛኅ ፡ አይደለም ፤ በማየ ፡ ገቦ ፡ ነው ፡ እንጅ ። በደመ ፡ ላሕም ፡ በደመ ፡ በግዕ ፡ አይደለም ፡ በደመ ፡ ገቦ ፡ ነው ፡ እንጅ ። በመንፈስ ፡ ረድኤት ፡ አይደለም ፡ በመንፈስ ፡ ልደት ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፴፬ ።

፯ ፤ እስመ ፡ ሠለስቱ ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ ይከውኑ ፡ ስምዐ ፡

ምስክር ፡ የሚሆኑ ፡ እሊህ ፡ ሦስቱ ፡ ናቸውና ፡ አላ ፡ በማይኒ ፡ ወበደምኒ ፡ ወበመንፈስኒ ፡ ሳለው ፡ መንፈስ ፡ ወማይ ፡ ወደም ፡ ማንሻ ፡ አንድም ፡ ምስክር ፡ የሚሆኑ፡ እሊህ ፡ ሦስቱ ፡ ማይ ፡ ደም ፡ መንፈስ ፡ ናቸውና ፡ አላ ፡ በማይኒ ፡ ወበደምኒ ፡ ወበመንፈስኒ ፡ ሳለው ፡ ወሠለስቲሆሙ ፡ ማንሻ ፡ ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፲፱ ፡

፰ ፤ መንፈስ ፡ ወማይ ፡ ወደም ።

ምስክር ፡ የሚሆኑ ፡ እሊህ ፡ ሦስቱ ፡ መንፈስ ፡ ማይና ፡ ደም ፡ ናቸውና ፡

ወሠለስቲሆሙ ፡ አሐዱ ፡ እሙንቱ ።

ሦስቱም ፡ አንድ ፡ ናቸው። (ሐተታ) ፡ ሦስቱን ፡ ሁሉ፡ አንድ፡ ሰው፡ ይቀበላቸዋልና፡ ባንድ ፡ ቄስ ፡ እጅ ፡ ሲሰጡ ፡ ይኖራሉና ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ይሰጣሉና ፡ ካንድ ፡ ከጌታ ፡ ተገኝተዋልና ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ተገኝተዋልና ፡ አንድ ፡ ክብር ፡ ያሰጣሉና ፡ አሐዱ ፡ እሙንቱ ፡ አለ ።

፱ ፤ ወእመሰ ፡ ስምዐ ፡ ሰብእ ፡ ንነሥእ ፡ ስምዐ ፡ እግዚአብሔር ፡ የዐቢ ።

የሰውንስ ፡ ምስክርነት ፡ የምንቀበል ፡ ከሆነ ፡ የእግዚአብሔርማ ፡ ምስክርነት ፡ እንደምን ፡ አይበልጥ ፡

ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ስምዑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

የእግዚአብሔር ፡ ምስክርነት ፡ ይህች ፡ ናት ፡

እንተ ፡ ስምዐ ፡ ኮነ ፡ ላዕለ ፡ ወልዱ ።

ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ብሎ ፡ ለልጁ ፡ የመሰከራት ፡ ምስክርነት ፡ ናት ፡ ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፲፯ ።

፲ ፤ ዘየአምን ፡ በወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሀለወ ፡ ስምዐ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌሁ ፡

በወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያመነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምስክርነቱ ፡ (ቦቱ) ፡ በሱ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡

ወዘሰ ፡ ኢየአምን ፡ በወልዱ ፡ ሐሳዌ ፡ ረሰዮ ፡

በባሕርይ ፡ ልጁ ፡ የማያምን ፡ ግን ፡ አብን፡ ሐሰተኛ ፡ አደረገው ፡

እስመ ፡ ኢአምነ ፡ በስምዕ ፡ እንተ ፡ ስምዐ ፡ ኮነ፡እግዚአብሔር ፡ ለወልዱ ።

እግዚአብሔር ፡ ለልጁ ፡ በመሰከረው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ምስክርነት ፡ አላመነምና ፡ ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፲፮፡፡ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፴፮ ፡፡

፲፩ ፤ ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ስምዑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

የእግዚአብሔር ፡ ምስክርነቱ ፡ ይህች ፡ ናት ፡

እስመ ፡ ወሀበነ ፡ ሕይወተ ፡ ዘለዓለም ፡

የዘለዓለም ፡ ድኅነትን ፡ የሰጠን ፡ መስጠት ፡ ናት ፡

ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ሕይወት ፡ እንተ ፡ በወልዱ ፡

ይህችውም ፡ የዘለዓለም ፡ ድኅነት ፡ በልጁ ያገኘናት ፡ ናት ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፬ ፡፡

፲፪ ፤ ዘሀለወ ፡ ምስሌሁ ፡ ወልድ ፡ ቦቱ ፡ ሕይወት ፡፡

ወልድ ፡ በሕልውናው ፡ ላለ ፡ ለአብ ፡ ሕይወትነት ፡ አለው ፡፡ አንድም ፡ ሕይወት ፡ የባሕርዩ ፡ ነው ፡፡ አንድም ፡ አብ ፡ በሕልውና ፡ ላለ ፡ ለወልድ ፡ ሕይወትነት ፡ አለው ፤ ሕይወት ፡ የባሕርዩ ፡ ነው ፡፡ አንድም ፡ ወልድ ፡ ላደረበት ፡ ለም እመን ፡ ሕይወት ፡ አለው ፡

ወዘሰ ፡ ኢሀሎ ፡ ምስለ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልቦቱ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡፡

ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያላደረበት ፡ ግን፡ የዘለዓለም ፡ ድኅነት ፡ የለውም ፡፡

፲፫ ፤ ወዘንተ ፡ ጸሐፍኩ ፡ ለክሙ ፡፡

ይህን ፡ ጻፍሁላችሁ ፡

ከመ ፡ ታእምሩ ፡ ከመ ፡ ብክሙ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡ እለ ፡ ተአምኑ ፡ በስሙ ፡ ለወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡፡

በወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ላመናችሁ ፡ ለናንተ ፡ የዘለዓለም ፡ ድኅነት ፡ እንዳላችሁ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡፡

፲፬ ፤ ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ እንተ ፡ ብነ ፡ ገጽ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡

ራሱን ፡ ከነቢያት ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ይናገራል ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያለችን፡ ባለሟልነት ፡ ይህች ፡ ናት ፡

እስመ፡ ዘሰአልነ፡ ኀቤሁ፡ በስመ፡ ዚአሁ፡ ይሰምዐነ ፡፡

ፊት ፡ እዴከ ፡ አንሥእ ፡ ኃይለከ ፡ ብለን ፡ የለመንነውን ፡ ልመና ፡ ሰምቶናልና፡ም ፡ ፪ ፡ ፳፰ ፡ ፫ ፡ ፳፩ ፡፡ ኤፌ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ፡፡ ዕብ ፡ ፬ ፡ ፲፮ ፡፡

፲፭ ፤ ወእመሰ፡ ርኢነ፡ ከመ፡ዘሰአልናሁ፡ይሰምዐነ ፡፡

ከዚህም ፡ ቀደም ፡ ፊት ፡ እዴከ ፡ አንሥእ ፡ ኃይለከ ፡ ብለን ፡ የለመንነውን ፡ እንዲሰማን ፡ ካወቅንስ ፡

ነአምር ፡ እንከ ፡ ከመ ፡ ብነ ፡ ስእለት ፡ ዘሰአልነ ፡ በኀቤሁ ፡፡

ዛሬም ፡ በቅንው ፡ ወልድከ ፡ በስቁል ፡ ወልድከ ፡ ብለን ፡ የምንለምነውን ፡ እንዲሰማን ፡ እናውቃለን ፡፡ አንድም ፡ (ወዛቲ ፡ ይእቲ) ፡ ራሱን ፡ ከሐዋርያት ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ይናገራል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያለችን ፡ ባለሟልነት ፡ ይህች ፡ ናት ፡ (እስመ፡ ዘሰአልነ) ፡ ዛሬ ፡ በስቁል ፡ ወልድከ ፡ በቅንው ፡ ወልድከ ፡ ብለን ፡ የለመንነውን ፡ ሰምቶናልና ፡ (ወእመሰ ፡ ርኢነ) ፡ ዛሬ ፡ በስቁል ፡ ወልድከ ፡ በቅንው ፡ ወልድከ ፡ ብለን ፡ የለመንነውን ፡ እንደ ፡ ሰማን ፡ ካወቅነስ ፡ እንግዴህም ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ በስቁል ፡ ወልድከ ፡ በቅንው ፡ ወልድከ ፡ ብለን ፡ የምንለምነውን ፡ እንዲሰማን ፡ እናውቃለን ፡

፲፮ ፤ ወእመሰ ፡ ቦ ፡ ዘርእዮ ፡ ለካልዑ ፡ እንዘ፡ ይኤብስ ፡ አበሳ ፡ ዘኢኮነ ፡ ለሞት ፡

ወንድሙን ፡ ለሞት ፡ የማያበቃ ፡ በደል ፡ ሲበድል ፡ ያየው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡

ለይስአሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ያሕይዎ ፡ ለዘይኤብስ ፡ አበሳ ፡ ዘኢኮነ፡ ለሞት ፡

ለሞት ፡ የማያበቃ ፡ በደል ፡ የበደለ ፡

www.ethiopianorthodox.org



ወንድሙን ፡ ያድነው ፡ ዘንድ ፡ እግዚአ አብሔርን ፡ ይለምንለት ፡

እስመቦ ፡ አበሳ ፡ ዘለሞት ፡፡

ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ በደል ፡ አለና ፡

ወኢኮነ፡በእንቲአሁ፡ ዘእብል፡ ከመ፡ ይስአሉ፡ ሎቱ ፡፡

ለዚያ ፡ ይለምኑለት ፡ የምል ፡ አይደለም ፡ ማቴ ፡ ፲፪ ፡ ፴፩ ፡፡

፲፯ ፤ እስመ ፡ ኵሉ ፡ አበሳ ፡ ኃጢአት ፡ ይእቲ ፡፡

ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡፡

ወቦ ፡ ጊጋይ ፡ ዘኢኮነ ፡ ለሞት ፡፡

ለሞት ፡ የማያበቃ ፡ በደል ፡ አለና ፡ ለዚያ ፡ ይለምኑለት ፡ አልሁ ፡ እንጅ ፡፡ ሐተታ፡ አበሳ ፡ ዘለሞት ፡ በአራቱ ፡ ውግረት ፡ ስቅለት ፡ ነው ፡ ዘኢኮነ ፡ ለሞት ፡ ግርፋት ፡ ከብት ፡ መክፈል ፡ ነው ፡ በሐዲሱ ፡ አበሳ ፡ ዘለሞት ፡ በውግዘት ፡ ዘኢኮነ፡ ለሞት፡ በቀኖና ፡ መለየት ፡፡ አንድም ፡ ዘለሞት ፡ ክህደት፡ ዘኢኮነ፡ ለሞት ፡ ኃጢአት ፡፡ አንድም ፡ ዘለሞት ፡ የነቢብ ፡ የገቢር ፡ ኃጢአት ፡ (ዘኢኮነ) ፡ የሐልዮ፡ ኃጢአት ፡፡ አንድም ፡ ዘለሞት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ካመኑ ፡ ከተጠመቁ ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ ምግባር ፡ ያሻል ፡ ማለት ፡ ገድል ፡ መወሰን ፡ (ጥቅ) ፡ እስመ ፡ ዘይዌስን ፡ ገድለ ፡ ለርእሱ ፡ ይመስል ፡ ብእሴ ፡ ዘየኀድር ፡ ቤተ ፡ ፈቂር ፡ እንዲል ፡ አበሳ ፡ ዘለሞት ፡ አንድ ፡ ጊዜ፡ ኃጢአት ፡ ስትሰረጀው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እሱ ፡ ሲሰረጃት ፡ (ጥቅ) ፡ ስብዐ ፡ ይወድቅ ፡ ኃጥእ ፡ ወስብዐ ፡ ይትነሣእ ፡ እንዲል ፡፡

፲፰ ፤ ነአምር ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ዘተወልደ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ኢይኤብስ ፡

ከእግዚአብሔር ፡ የተማረ ፡፡ አንድም ፡ የተወለደ ፡ እንዳይበድል ፡ እናውቃለን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢበድል ፡ ሁለተኛ ፡ በሐልዮ ፡ ቢበድል ፡ በነቢብ ፡ በገቢር ፡ አይበድልም ፡

አላ፡ ዘተወልደ፡ እምእግዚአብሔር፡ የዐቅብ ፡ ርእሶ ፡

ከእግዚአብሔር፡ የተማረ ፡፡ አንድም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተወለደ ፡ ራሱን ፡ ከኃጢአት ፡ ይከለክላል ፡ እንጂ ፡

ወእኩይኒ ፡ ኢይሐስጦ ፡፡

ፈቃደ ፡ ሥጋ ፡፡ አንድም ፡ ፈቃደ ፡ ሰይጣን ፡ ድል ፡ አይነሣውም ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፱ ፡፡ ፪ ፡ ተሰ ፡ ፫ ፡ ፫ ፡፡

፲፱ ፤ ነአምር ፡ ከመ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ንሕነ ፡

እኛ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተማርነ ፡፡ አንድም ፡ የተወለድነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እናውቃለን ፡

ወዓለምሰ ፡ ኵሉ ፡ በእኪት ፡ ይቀውም ፡፡

ዓለሙ ፡ ግን ፡ በክፋት ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ ገላት ፡ ፩ ፡ ፬ ፡፡

፳ ፤ ወነአምር ፡ ከመ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መጽአ ፡ ወወሀበነ ፡ ልበ ፡

ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ እንዳስተማረን ፡ እናውቃለን ፡

ከመ ፡ ናእምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘበጽድቅ ፡

የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብን ፡ እናውቀው ፡ ዘንድ ፡

ወሀለውነ ፡ በአሚን ፡ በወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡፡

የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ የሚሆን ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፤ በማመን፡ ጸንተን ፡ እንኖራለን ፡፡ አንድም፡ እንድንኖር ፡ እናውቃለን ፡

ውእቱ ፡ ዘበአማን ፡ እግዚአብሔር ፡፡

ይኸውም ፡ እውነተኛ ፡ የባሕርይ ፡ አም

ላከ ፡ የሚሆን ፡ ሐተታ ፡ አብን ፡ ዘበጽድ
ቅ ፡ ብሎ ፡ ነበረና ፡ ወልድን ፡ ዘበአማን ፡
አለ ፡ ለማስተካከል ። ዕሪናቸውን ፡ ለመ
ንገር ፡

ወብነ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ።

የዘለዓለም ፡ ድኅነትን ፡ የምናገኝባት ፡ ሃ
ይማኖት ፡ አለችን ፡

ባቲ፡ ደቂቀየ፡ ዕቀቡ፡ ርእሰክሙ፡ እምነ፡ አማልክት።

በሃይማኖት ፡ ከአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ተከል
ከሉ ። እንድም ፡ የዘለዓለም ፡ ድኅነትን ፡
የምናገኝባት ፡ ፍቅረ ፡ ቢጽ ፡ አለችን ፡
በፍቅረ ፡ ቢጽ ፡ ከፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ተከል
ከሉ ። እንድም ፡ የዘለዓለም ፡ ድኅነትን ፡
የምናገኝባት ፡ ንስሓ ፡ አለችን ፡ በንስሐ ፡
ከኃጢአት ፡ ተከልከሉ ፡ ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፫ ።
ሮሜ ፡ ፱ ፡ ፳፰ ። ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ። ዕብ ፡
፩ ፡ ፫ ። ዘፀአ ፡ ፳ ፡ ፫ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፲፬ ።

መልአት ፡ መልእክተ ፡ ዮሐንስ ፡ ቀዳሚት ፡ በሰላመ
እግዚአብሔር ።

መዠመሪያዪቱ ፡ የዮሐንስ ፡ ክታብ ፡ ፍ
ቅረ ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ፍቅረ ፡ ቢጽን ፡
ስትሰብክ ፡ ደረሰች ፡ ተፈጸመች ።

www.ethiopianorthodox.org